# ራፕሶዲ ኦፍ ሪያሊቲስ

...ዕለታዊ የመንፈሳዊ ጥናት መጽሃፍ

*Chris Oyakhilome*

LWPL LoveWorld Publishing

**በተለየ ሁኔታ ናልተጠቀሰ በስተቀር ሁለም ጥቅሶች ከመደበኛው የመጽሐፍ ቅዱስ የተወሰዱ ናቸው።**

ራፕሶዲ ኦፍ ሪያሊቲስ ...ዕለታዊ የመንፈሳዊ ጥናት መጽሃፍ

ISSN 1596-6984

መስከረም 2012 edition

Copyright © 2012 by LoveWorld Publishing

**ለበለጠ መረጃና ተጨማሪ ለማዘዝ:**

**UNITED KINGDOM:**
Unit C2, Thames View Business
Centre, Barlow Way Rainham-Essex,
RM13 8BT.
Tel.: +44 (0)1708 556 604
+44 (0)08001310604

**USA:**
Christ Embassy Houston,
8623 Hemlock Hill Drive
Houston, Texas. 77083
Tel.: +1(800) 620-8522

**NIGERIA:**
Plot 97, Durumi District, Abuja, Nigeria.

Plot 22/23 Billingsway Road, Oregun,
Ikeja, Lagos.
P.O. Box 13563 Ikeja, Lagos
Tel.: +234 1 8888186

**SOUTH AFRICA:**
303 Pretoria Avenue
Cnr. Harley and Braam Fischer,
Randburg, Gauteng 2194
South Africa.
Tel.:+27 11 326 0971

**CANADA:**
LoveWorld Publishing Canada
4101 Steeles Ave W, Suite 204
Toronto, Ontario
Canada M3N 1V7
Tel.:+1 416-667-9191

***www.rhapsodyofrealities.org***
***email: rorcustomercare@loveworld360.com***

All rights reserved under International Copyright Law. Contents and/or cover may not be reproduced in whole or in part in any form without the express written permission of LoveWorld Publishing.

# መግቢያ

የ2012 ዓ.ም. ተወዳጁ “ የራፕሶዲ ኦፍ ሪያሊቲስ “ እትም፣ የመንፈሳዊ ህይወትህ እርምጃና እድገት ለማሳደግ በተለየና ባማረ ሁኔታ ለተሻለ ነገር በሚያነሳሳ መልኩ የተዘጋጀ ነው፡፡ በመረጃና በመገለጥ ከተሞሉ ፁሁፎች በተጨማሪ የዚህ ወር ዕትም በየዕለቱ የእግዚአብሔርን መለኮታዊ መገኘት ለማወቅ በምታደርገው ጉዞ እምነትህን በእግዚአብሔር ቃል ላይ እንድታሳድግ በተመቻቸ ሁኔታ ተዘጋጅቶ ቀርቦልኃል፡፡ በየቀኑ ባጠናኸው፣ ባሰላሰልከውና በአፍህ በተናገርከው ወይም ደግሞ ባወጅከው መጠን እየታደስክ ትሄዳለህ፡፡

## - ይህንን መነቃቅያ እንዴት በበለጠ መጠቀም ይቻላል -

- ይህን ጽሁፍ አንብብና በጥንቃቄ አሰላስል፡፡ ፀሎቶቹንና የአፍ ምስክርነት ቃሉን በየቀኑ ለራስህ ድምጽህን ጎላ አድርገህ መናገርህ የእግዚአብሔር ቃል በሕይወትህ እንዲያልፍ ያደርጋል፡፡
- የአንድ ዓመት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ወይም በአዲሱ የሁለት ዓመት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት በሚገባ አንብቡ
- የዕለታዊው የመጽሐፍ ቅዱስ ንባቡን በጠዋትና በማታ ከፍለህ ማንበብ ትችላለህ
- መነቃቅያውን በጸሎት ተጠቀሙበትና በእያንዳንዱ ወራት ያላችሁን ግብ ጻፉና ከአንዱ ግብ ወደ ሌላው ግብ ያላችሁን ስኬት በሚገባ ለኩ

የእግዚአብሔርን ቃል በየቀኑ በወሰድን ጊዜ የእግዚአብሔርን የክብር መገኘትና ድል ዓመቱን በሙሉ እንዲደሰቱበት ጥሪ እናደርጋለን፡፡ በጣም እንወዳችኋለን፡፡ እግዚአብሔር ይባርካችሁ!

-ፓስተር ክሪስና አያኪሎሜ

## የግል መረጃ

ስም

አድራሻ

ስልክ

# ራፕሶዲ ኦፍ ሪያሊቲስ

...ዕለታዊ የመንፈሳዊ ጥናት መጽሃፍ

www.rhapsodyofrealities.org




ማክሰኞ 1

# ለክርስቶስ ኑሩ

> በፊታችሁ ሕይወትንና ሞትን በረከትንና መርገምን እንዳስቀመጥኩ እኔ ዛሬ ሰማይንና ምድርን በአንተ ላይ አስመሰክራለሁ፤እንግዲህ አንተና ዘርህ በሕይወት ትኖሩ ዘንድ ሕይወትን ምረጥ ። (ዘዳግም 30፡19)

ስለ መነጠቅና ስለ ዘላለም ዋስትናቸው እርግጠኛ ባለመሆን የሚጨነቁ አንዳንድ ክርስቲያኖች አሉ፡፡ ጌታ በእንደዚህ አይነት ፍርሃትና ጭንቀት እንድንኖር ፈፅሞ አይፈልግም፡፡ እውነታው ዘላለማዊ ዋስትና ዳግም ለተወለዱ ሁሉ ተጨባጭ የሆነ መሆኑ ነው፤ ነገር ግን ዋስትናቸው እስከ ፍፃሜ ድረስ በክርስቶስ ሕይወትና በጽድቁ በመኖር ይወሰናል፡፡

ለምሳሌ አንድ ሰው ዳግም ቢወለድና ከተወሰነ ጊዜ በኋላ ኢየሱስን መከተል ቢያቆም ከእግዚአብሔር ጋር ያለው ዘላለማዊ ዋስትና አደጋ ላይ ስለሚወድቅ ይህ ሰው ችግር ላይ ነው፡፡ ዳግም ስትወለዱ በእግዚአብሔር መገኘት ውስጥ ነው የተወለዳችሁት፣ በእርሱ ህልውና ውስጥ ነው የምትኖሩት፡፡ እርሱ ከለላችሁ ነው፡፡ እንደ መጽሐፍ ቅዱስ አስተምህሮ እርሱ ጠባቂያችሁ ነው፣ ማንም ከእጁ ሊያወጣችሁ አይችልም፡፡

ነገር ግን ሕይወት በምርጫ የተሞላ ነው፡፡ ያለማቋረጥ ለእርሱ ለመኖር መምረጥ የእናንተ ድርሻ ነው፡፡ እግዚአብሔር ሲመራን ምርጫን በፊታችን ያስቀምጣል፣ ምን መምረጥ እንዳለብንም ይነግረናል፡፡ የተሳሳተ ምርጫ ብንመርጥ የሚያስከትለውን ውጤት እንድንረዳ ቢያደርግም እንኳን እግዚአብሔር በምርጫችን ላይ ግን ፈፅሞ ተፅእኖ አያደርግም፡፡

ስለዚህ ማድረግ ያለባችሁ እንደ ቃሉ መኖር ነው፤ በጣም ቀላሉ ነገር ይህ ነው፡፡ ዳግም ስትወለዱ በውስጣችሁ ካለው የክርስቶስ ሕይወት የተነሳ ለክርስቶስ መኖር ቀላልና ተፈጥሯዊ ዝንባሌያችሁ ነው፡፡ በትክክል መኖር ተፈጥሯዊ ባህሪያችሁ በመሆኑ፣ የተሳሳተ ነገር ለማድረግ እጅግ ፈተና የሚሆንበት ተፈጥሮ ያላችሁ ናችሁ፡፡ የመንፈስ ቅዱስ አገልግሎትም

የሚያስፈልገው እናንተ በትክክል እንድትኖሩ ነው፡፡ የክርስትናን ሕይወት እንድትኖሩ መንፈስ ቅዱስ ይረዳችኋል፤ እርሱ በሕይወታችሁ ስላለ ፈፅሞ መንገዴን እስት ይሆን ብላችሁ አትጨነቁ፡፡

መጽሐፍ ቅዱስ በተጨማሪ እንዲህ ይላል፡- ‘‘ሳትሰናከሉም እንዲጠብቃችሁ፣በክብሩም ፊት በደስታ ነውር የሌላችሁ አድርጎ እንዲያቆማችሁ ለሚችለው’’(ይሁዳ 1፡24)፡፡ ለጌታ ስትኖሩ በጋለ ስሜት ከፅኑ እምነት ጋር ስታገለግሉት እርሱ በሕይወታችሁ ያለውን እቅድና አገልግሎት ይፈፅማል፡፡

## የእምነት አዋጅ

በክርስቶስ ኢየሱስ ያለኝን አገልግሎቴንና ጥሪዬን እየፈጸምኩ በአላማ እኖራለሁ፡፡ ከጌታና ከዘላለማዊ መንግስቱ ትኩረቴን የሚወስድ ማንኛውንም ነገር እቃወማለሁ፡፡ ለስራ ከመትጋት አልለግምም፣ በመንፈስ የተቃጠልኩ ነኝ፣ ጌታን እያገለገልኩ የሕይወቴን መስመርና ከጌታ ኢየሱስ የተቀበልኩትን የእግዚአብሔር ፀጋ የሆነውን ወንጌል የመመስከር አገልግሎት በደስታ እፈጽማለሁ፡፡ ሀሌሉያ!

## ለተጨማሪ ጥናት:

2 ኛ ጴጥሮስ 1:5-11; 2 ኛ ቆሮንጦስ 5:15

### የአንድ ዓመት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት

1 ኛ ቆሮንጦስ 15:35-58 & መጽሀፈ ምሳሌ 8-9

### የሁለት ዓመት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት

1 ኛ ተሰሎንቄ 2:10-20 & ትንቢተ ኤርምያስ 18

**Leave comments on today's devotional at**
***www.rhapsodyofrealities.org***





# እምነታችሁ መሳሪያ ነው

> እርሱም፦እምነታችሁ የት ነው?አላቸው፡፡ ፈርተውም ተደነቁ፤እርስ በርሳቸውም፦እንዲህ ነፋሳትንና ውኃን እንኳ የሚያዝ ለእርሱም የሚታዘዙለት ይህ ማን ነው?አሉ። (ሉቃስ 8፡25)

አንድ ቀን ኢየሱስ ከደቀ-መዛሙርት ጋር በጀልባ ነበር፤አውሎ ነፋስም ተነሳ፡፡ደቀ-መዛሙርትም ፈሩ መፅሀፍም እንዲህ ይላል “ቀርበውም፦አቤቱ፤አቤቱ ጠፋን እያሉ አስነሱት፡፡እርሱም ነቅቶ ነፋሱንና የውኃውን ማዕበል ገሰጻቸው፤ተውም፤ጸጥታም ሆነ”(ሉቃስ 8፡24)፡፡

ጌታም ወደ ደቀ-መዛሙርቱ ዞሮ “እምነታችሁ ወዴት አለ?”በማለት ወሳኝ ጥያቄ ጠየቃቸው፡፡ በሕይወት ውስጥ ትልቁ ጥያቄ ይሄ ነው፡፡ በእምነታችሁ ሁሉን ነገር ማድረግ ትችላላችሁ፤ ተራሮችን ማንቀሳቀስ ትችላላችሁ፤ታላላቅ ውጤቶችን ማምጣት ትችላላችሁ፡፡እምነት መሳሪያ ነው፤ተጠቀሙበት፡፡ እምነታችሁን መጠቀም ብትማሩ በየቀኑ በድል ትኖራላችሁ፡፡

ለእርዳታ መጮኽ አቁሙ! ሕይወታችሁን የከበረ ለማድረግ እምነታችሁን ተጠቀሙ፡፡ በእምነታችሁ ካንሰርን፤የስኳር በሽታንና የልብ ህመምን ማጥፋት ትችላላችሁ፡፡በሕይወታችሁ ያለውን ሁኔታ መለወጥ ትችላላችሁ! እምነታችሁን ገንቡት፡፡ የእግዚአብሔርን ቃል በመማርና በመኖር እምነታችሁን ለመመገብ ወስኑ፡፡

መጽሐፍ ቅዱስ በነቢያትና በሀዋርያት በኩል የተሰጠን መለኮታዊ መገለጥን የያዘ መፅሀፍ ነው፡፡መልእክቶቹ ተደጋግመው የተረጋገጡ ናቸው፡፡በጤናችሁ፤በቤተሰባችሁ፤በገንዘባችሁ፤በስራችሁ፤በትምህርታችሁ፤በአገልግሎታችሁ እምነታችሁን በማሳደግና በየዕለቱ እንዲሰራ በማድረግ በክብር በአሸናፊነት መኖር ትችላላችሁ፡፡ አስታውሱ፤አለምን የሚያሸንፈው እምነታችን ነው (1ኛ ዮሀንስ 5፡4)

## የእምነት አዋጅ

በእምነቴ እግዚአብሔር ለወሰነልኝ የድል፣የስኬት፣የደስታ፣የጤናና የብልጽግና ሕይወት በመኖር ሕይወቴን በክብርና በልቀት ጎዳና እንዲሄድ በጽናት ቅርጽ አስይዛለሁ፡፡በዚህ ሕይወት ተጎጅነትንና ረዳት የለሽነትን እቃወማለሁ፡፡በቃሉ ላይ ያለኝ እምነት ውጤታማና አሸናፊ ነው፡፡ እግዚአብሔር ይመስገን!

## ለተጨማሪ ጥናት:

1 የዮሐንስ ወንጌል 5:4; ዕብራውያን 10:38-39; የማቴዎስ ወንጌል 17:20

### የአንድ ዓመት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት

1 ኛ ቆሮንጦስ 16:1-24 & መጽሀፈ ምሳሌ 10-11

### የሁለት ዓመት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት

1 ኛ ተሰሎንቄ 3:1-13 & ትንቢተ ኤርምያስ 19-20

**Leave comments on today's devotional at**
***www.rhapsodyofrealities.org***





# የግል የጸሎት ልምድ ይኑራችሁ

> እናንተም ትጠሩኛላችሁ፣ሄዳችሁም ወደ እኔ ትጸልያላችሁ፣ እኔም እሰማችኋለሁ ።
> (ኤርሚያስ 29፡12)

ከላይ ባለው ጥቅስ እንደነገረን ጌታ እንድንጸልይ የጠራን ሊመልስልን ስላቀደ ነው፡፡ ስለዚህ የጸሎት ዕቅድ ሊኖራችሁ ያስፈልጋል፡፡ የጸሎት ዕቅድ ከሌላችሁ የመጸለይ እድላችሁ አጠራጣሪ ነው፡፡ ጊዜያችሁን የሚይዙና እንዳትጸልዩ የሚከለክሏችሁ ብዙ ድርጊቶች ይኖራሉ፡፡ የጸሎት ባህልና ልምድ እንዲኖራችሁ አስፈላጊውን ጥረት ማድረግ አለባችሁ፤እንዲህ ለማድረግ የማንቂያ ደወል ማድረግ ትችላላችሁ። ለመጸለይ ባተሌ አትሁኑ፡፡

ጸሎት የሆነ ነገር ከእግዚአብሔር ስትፈልጉ ብቻ የሚደረግ አይደለም። ጸሎት ለጌታና ከጌታ ጋር የምታወሩትና፣ በመንፈሳችሁ ለእናንተ የሚናገረውን ለመስማት ለእሱ አትኩሮት የምትሰጡበት ህብረት ነው፡፡ ማንኛውም ክርስቲያን የጸሎት ጊዜ ሊኖረው ይገባል፡፡

በቋሚነት የጸሎት ጊዜ እንዳይኖራችሁ ተግዳሮት ካለባችሁ፣የግል የጸሎት መርሃ-ግብር እቅድ ማውጣት እንድትችሉ ጌታ እንዲመራችሁ ጠይቁት፡፡ ችላ አትበሉ፡፡ በቤተ-ክርስቲያን ወይም በቡድን ተሳታፊ የምትሆኑባቸው የጸሎት ፕሮግራሞችና አገልግሎቶች አሉ፤ ይህ ግን ከግል የጸሎት ጊዜያችሁ የተለየ ነው፡፡

አንድ ሰው “በየቀኑ ሳይሆን በሳምንት አንድ ቀን እጸልያለሁ” ሊል ይችላል፡፡ በፍጹም ይህ በቂ አይደለም፡፡ በየቀኑ የጸሎት ጊዜ ሊኖራችሁ ይገባል፤ ምክንያቱም በየቀኑ የመንፈሳዊ ንቃት እንዲኖራችሁ ይረዳችኋል። “ታዲያ ምን ያህል መጸለይ ነው ያለብኝ?” ትሉ ይሆናል፡፡

ምን ያህል መጸለይ እንዳለባችሁ ሌላ ሰው መወሰን የለበትም፤ ነገር ግን ጸሎት በእናንተና በጌታ መካከል ያለ ግንኙነት ስለሆነ በበቂ ሁኔታ

ካልጸለያችሁ ራሳችሁ ታውቃላችሁ፡፡ በቂ ጸሎት እንዳልጸለያችሁ ካሰባችሁ ተጨማሪ ሰዓት ጸልዩ፡፡ እውነታው ብዙ ሰዓት ስትጸልዩ የተሻለ ጥቅም ታገኛላችሁ ምክንያቱም ከጌታ ጋር ከማውራታችሁም በላይ መንፈሳችሁ ይታነጻል፡፡

ይህ ብቻ አይደለም ስትጸልዩ መንፈሳችሁ ይሰለጥናል፡፡ ማንም የመንፈስ ቅዱስን ያህል የሚያስተምራችሁ የለም፡፡ በዚያ የፀሎት ከባቢ ውስጥ ያስተምራችኋል፤ሊመራችሁና ብርሀን ሊሰጣችሁ የሚችልን መረጃ ያመጣላችኋል፡፡ ክብር እግዚአብሔር ይሁን!

## ጸሎት

ውድ አባት ሆይ፣በጸሎት ከአንተ ጋር የማያቋርጥ ህብረት እንዲኖረኝ ስለሰጠኸኝ ዕድል አመሰግናለሁ፡፡ የጸሎት ልምድ አለኝ፣አሁን እንኳ የክርስቶስን ወንጌል ተቀብለው እንዲድኑ ልባቸው እንዲከፈት በአለም ዙሪያ ላሉ ላልዳኑ ነፍሳት እጸልያለሁ፡፡የፈውስ፣የመጠገን፣የመዳን ሀይል የሚያደርግ ታላቅ ጸጋ በስጋ ህመም ውስጥ ላሉ ክርስቲያኖች እንዲሆንላቸው እጸልያለሁ፤በጌታ በኢየሱስ ስም፡፡አሜን፡፡

## ለተጨማሪ ጥናት:

የሉቃስ ወንጌል 18:1; የያዕቆብ መልእክት 1:20; ኤፌሶን 6:18

**የአንድ ዓመት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት**

2 ኛ ቆሮንጦስ 1-2:1-4 & መጽሀፈ ምሳሌ 12-13

**የሁለት ዓመት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት**

1 ኛ ተሰሎንቄ 4:1-8 & ትንቢተ ኤርምያስ 21

**Leave comments on today’s devotional at**
***www.rhapsodyofrealities.org***



አርብ 4

# እራሳችሁን በቃሉ ውስጥ ተመልከቱ

> እንግዲህ በክርስቶስ ኢየሱስ ላሉት አሁን ኩነኔ የለባቸውም ። (ሮሜ 8፡1)

በመክፈቻ ጥቅሳችን መንፈስ ቅዱስ በሐዋርያው ጳውሎስ በኩል ሁለት አይነት ቡድኖች አሉ እያለን አይደለም፤ በክርስቶስ ኢየሱስ ሆነው በስጋ ፈቃድ የሚመላለሱ እና በስጋ ፈቃድ የማይመላለሱ፡፡ የመልዕክቱ ፍሬ ነገር እንደዚያ አይደለም፣ ይልቁን የእውነተኛ ማንነታችሁን ስዕል እያሳያችሁ ነው፡፡

አዲስ ኪዳንን ስታጠኑና ስትረዱ "የመስታዎት መርህ" የሚለውን ታጤናላችሁ፤ የእግዚአብሔር ቃል መስታወታችሁ ነው፡፡ እናንተ በቃሉ ውስጥ የምታዩትን ናችሁ (2ኛ ቆሮንቶስ 3፡18)፡፡ ስለዚህ አንዳንዴ ስህተት ስለምትሰሩ የመክፈቻ ጥቅሳችንን አንብባችሁ በቃ ከኩነኔ ነጻ አይደለሁም ወይም "በስጋ ነው የምመላለሰው" ብላችሁ ታስባላችሁ፡፡ በፍጹም እንደዚያ ግን አይደለም፡፡

በዚያው ምዕራፍ ላይ ቁጥር 9ኝን አንብቡ፤ በግልፅ እንዲህ ያብራራልናል "እናንተ ግን የእግዚአብሔር መንፈስ በእናንተ ዘንድ ቢኖር፣ በመንፈስ እንጅ በሥጋ አይደላችሁም...."(ሮሜ 8፡9) እየተናገረ ያለው እግዚአብሔር ነው! እግዚአብሔር በክርስቶስ ኢየሱስ በመንፈስ እንጅ በስጋ ስለማይመላለሱ ሲናገር የተናገረው ስለእናንተ ነው፡፡

ስለዚህ ራሳችሁን በቃሉ ውስጥ ተመልከቱ፡፡ እናንተ ዳግም ተወልዳችኋል፣ ኩነኔ ፈጽሞ የለባችሁም፡፡ ይህን ስትረዱና እንደዚያም ስትኖሩ ከሀጢያት ልምምድ፣ ከክፉ ሀሳብ ወይም ከስጋ ስራ ጋር ትግላችሁን ታቆማላችሁ፡፡ ሮሜ 6፡14 "ኃጢአት አይገዛችሁም"ይላል፡፡ እግዚአብሔር እንዲህ ስለሆነ የሚያያችሁ ራሳችሁን እንዲሁ ተመልከቱ፡፡

እግዚአብሔር እንደሚያያችሁ ራሳችሁን ብትመለከቱ እንደዚያው ትኖራላችሁ፡፡ እንድትሆኑ ያደረጋችሁን ተቀበሉ፣ በክርስቶስ ኢየሱስ የእርሱ

ጽድቅ ናችሁ፣ እንደዚያም ተመላለሱ፡፡ ክብር ለእግዚአብሔር!

## የእምነት አዋጅ

በመንፈሴ ውስጥ የእግዚአብሔር ሕይወት ያለኝ የእግዚአብሔር ልጅ ነኝ፡፡ያለ ጥፋተኝነት፣ፍርሃት ፣የበታችነት ወይም ኩነኔ በእግዚአብሔር ፊት ፀድቄያለሁ፡፡ኃጢአት ፈጽሞ አይገዛኝም፣ በየትኛውም አይነት ቀንበር አልያዝም፡፡የጽድቅ ተፈጥሮዬን አውቃለሁ፣እንደዚያም እመላለሳለሁ፡፡ ክብር ለእግዚአብሔር!

## ለተጨማሪ ጥናት:

ሮሜ 6:11-15; ሮሜ 8:2-4; ገላትያ 2:20-21

የአንድ ዓመት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት

2 ኛ ቆሮንጦስ 2:5-3:1-6 & መጽሀፈ ምሳሌ 14-15

የሁለት ዓመት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት

1 ኛ ተሰሎንቄ 4:9-18 & ትንቢተ ኤርምያስ 22

**Leave comments on today's devotional at**
***www.rhapsodyofrealities.org***





# ለወንጌል እውነተኛ ሁኑ

> በሁሉ እንገፋለን እንጅ አንጨነቅም፤እናመነታለን
> እንጅ ተስፋ አንቆርጥም ።
> (2ኛ ቆሮንቶስ 4፡8NLT)

ዛሬ እኛ ያለን ክርስትና፣ በወርቅ ገበታ ላይ ሆኖ ወይም በቀላሉ የመጣ አይደለም፡፡ ስለ ክርስቲያን ሰማዕታት ብታነቡ ብዙዎች ስለ ክርስቶስ በመመስከራቸው እንደተገደሉና አንገታቸው እንደተቀላ ታያላችሁ፡፡ በአንድ አጋጣሚ ከስድስት ሺህ በላይ የሆኑ ሰዎች በኢየሱስ ክርስቶስ ባላቸው እምነት ምክንያት ታርደዋል፣ እነዚያም ወታደሮች ነበሩ፡፡ ወንጌልን በሙሉ ልባቸው አምነዋል፣ የተቀበሉትን እምነት ወደሚቀጥለው ትውልድ ለማስተላለፍ አንዳች የሚያቆማቸው ኃይል አልነበረም፡፡

በአመታት ውስጥ ጌታን ለማምለክ፣ በቤተ-ክርስቲያን እርሱን ለማመስገን፣ በታላላቅ ጉባኤዎች ለመታደምና ሕይወትን በሚቀይሩ ውይይቶች ላይ እንድትሳተፉ ያገኛችሁትን ነጻነት እንድትጎናጸፉ በጥልቅ ትግል፣ በጸሎት፣ በእምባ፣ በደም፣ በእምነት፣ በጽናትና በጋለ ስሜት ሕይወታቸውን ለወንጌል መስዋዕት ባደረጉ ወንዶችና ሴቶች የመጣ ነፃነት ነው፡፡ ስደት ብቻ አይደለም የሆነባቸው፣ በሕይወት እያሉም ተቀብረዋል። አንዳንዶች በኢየሱስ ክርስቶስ ባላቸው እምነት በመጋዝ ለሁለት ተሰንጥቀዋል፣ በጭካኔም ተገድለዋል፡፡

ዛሬም በብዙ ሀገራት ክርስቲያኖች ስደትና ጭፍጨፋ ያጋጥማቸዋል። አንዳንድ ሀገራት ክርስቲያኖች በኢየሱስ ላይ ባላቸው እምነት ምክንያት መጥፎና አሰቃቂ እንግልት የሚፈጽሙበት የማጎሪያ ስፍራ አላቸው፡፡ በይፋ የወጣ የቅርብ ጊዜ ሪፖርት እንደሚያሳየው በአለም ላይ ከፍተኛ ግፍና ጭፍጨፋ ከሚያጋጥማቸው ቡድኖች ክርስትያኖች በዋነኛነት ይጠቀሳሉ፡፡

ይህንን ጉዳይ እያሳየኋችሁ ያለሁት በኢየሱስ ክርስቶስ ያለን እምነት እንዲሁም ያመነው የክርስቶስ መልዕክት ሁሉ ነገር የሚገባው መሆኑን እንድትረዱት ነው፡፡ ምንም እንኳ ጭፍጨፋ ቢበዛም ከእኛ በፊት የነበሩት እምነታቸውን ጠብቀዋል፣ ለወንጌልም እውነተኞች ሆነው አልፈዋል፡፡

በእኛም ጊዜ እንዲሁ ሊሆን ይገባል፡፡

በከተማችሁ ወይም በአገራችሁ ምንም ነገር እየሆነ ቢሆን እንኳ ለክርስቶስ ታማኞች ሁኑ፡ ፡አታወላውሉ፡፡ በመከፈቻ ጥቅሳችን እንዳነበብነው አናቆምም፣ ተስፋም አንቆርጥም፡፡ በጊዜውም ያለጊዜውም ቃሉን ስበኩ፡፡ በአለም ካሉት ባላጋራዎችና መከራዎች ሁሉ ይልቅ በእናንተ ያለው እጅግ ታላቅ ነውና ጸጥ ሊያሰኛችሁ የሚችል ምንም አይነት አስፈሪና አስደንጋጭ ነገር የለም፡፡ ሀሌሉያ!

## የእምነት አዋጅ

በአለም ካለው መከራ፣ጭንቀት፣ስደት ወይም አደጋ ይልቅ በወደደኝ በእርሱ፣በጌታዬ በክርስቶስ ኢየሱስ ከአሸናፊዎች እበልጣለሁ፡፡ሞት ቢሆን፣ሕይወትም ቢሆን፣መላእክትም ቢሆኑ፣ግዛትም ቢሆን፣ኃይላትም ቢሆኑ ወይም የትኛውም ነገር ቢሆን በክርስቶስ ኢየሱስ ካለ ከእግዚአብሔር ፍቅር ሊለየኝ እንዳይችል ተረድቻለሁ፡፡የጸናሁ፣የማልነቃነቅ፣እስከ አለም ዳርቻ ወንጌልን የማድረስ ስራ ሁል ጊዜ ይበዛልኛል፡፡አሜን!

## ለተጨማሪ ጥናት:

ሮሜ 8:35-39; 1 ኛ ተሰሎንቄ 3:7-8 NLT

የአንድ ዓመት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት

2 ኛ ቆሮንጦስ 3:7-4:1-18 & መጽሀፈ ምሳሌ 16-17

የሁለት ዓመት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት

1 ኛ ተሰሎንቄ 5:1-11 & ትንቢተ ኤርምያስ 23

**Leave comments on today's devotional at**
***www.rhapsodyofrealities.org***



## እሁድ 6

# ቤተ ክርስትያን የእግዚአብሔር ሀብት ናት

> እኔም እልሃለሁ፣አንተ ጴጥሮስ ነህ፣በዚችም ዓለት ላይ ቤተ ክርስቲያኔን እሰራለሁ፣የገሃነም ደጆችም አይችሉአትም ። (ማቴዎስ 16፥18)

በማቴዎስ 13፥44 ኢየሱስ እንዲህ አለ “ደግሞ መንግስተ ሰማያት በእርሻ ውስጥ የተሰወረውን መዝገብ ትመስላለች፤ሰውም አግኝቶ ሰወረው፣ከደስታውም የተነሣ ሄዶ ያለውን ሁሉ ሸጠና ያን እርሻ ገዛ”፡፡ በእርሻ ውስጥ ካለው ሀብት የተነሳ ኢየሱስ ምድርን ሁሉ ገዛ፡፡ ሀብቱ ቤተ ክርስቲያን ስትሆን እርሻው ደግሞ አለም ናት፡፡

ኢየሱስ ከቤተ ክርስቲያን የተነሳ አለምን በገዛ ደሙ ገዝቷል፤ስለ ቤተ ክርስቲያን ሁሉን ነገር ሰቷል፡፡ይህ እውነት ሰይጣን ምን እንደሚፈልግ ይነግረናል፡፡በአለም ላይ ችግርን ሲፈጥር ወይም ሲያነሳሳ ዓይኖቹ በእግዚአብሔር ልጆች ላይ ነው፣በቤተ ክርስቲያን ላይ፡፡የእቅዱ ፍጻሜ ሁሌም በኢየሱስ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ላይ ነው፡፡ሁልጊዜም በነጻነት እግዚአብሔርን በሚያገለግሉና በሚያመልኩ የእግዚአብሔር ህዝብ ላይ ፍጹም የሆነ ጥላቻ አለበት፡፡ነገር ግን ፈጽሞ ተሳክቶለት አያቅም፡፡

ለምንድነው ሰይጣን የቤተ ክርስቲያን ተቃዋሚ የሆነው? ምክንያቱም ከመጀመሪያ ጀምሮ ሰይጣን የሚመኘውን፣ ቤተ ክርስቲያን ማለትም እኛ፣ እናንተና እኔ ስላለን ነው፡፡ በኢሳያስ 14፥14 “...በልዑልም እመሰላለሁ” ብሎ ነበር ግን አልቻለም፡፡ ይልቁንም ከገነት ተባረረ፡፡ ሰይጣን ኢየሱስ የሰራት ቤተ ክርስቲያን የእግዚአብሔርን ስም፣ ዙፋኑን፣ መቀመጫውን ተካፋይ እንደሆነች ተመለከተ!

ከክርስቶስ ፍቅር የተነሳ አሁን ከእግዚአብሔር ጋር አንድ ሆነናል፡፡ ኢየሱስ ቤተ ክርስቲያኔን እሰራለሁ የሲኦልም ደጆች አይቋቋሟትም ብሏል፤ ይህ ሊሻር የማይችል እውነት ነው፡፡ ሀሌሉያ! በፅንፈ-አለሙ ውስጥ ቤተ ክርስቲያንን የሚቋቋም አንዳች ሃይል የለም፡፡ ቤተ ክርስቲያንን እንደ ቀላል ተቋም አትመልከቱ፤ የተቀደሰች የክርስቶስ አካል ነች፡፡ እጅግ ውድ ዋጋ

ያላት የእርሱ እንቁ ነች፡፡

## የእምነት አዋጅ

የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን በታላቅ ክብር፣በሀያል ችሎታ እና በማይቆም ተፅዕኖ ለውጥ እያመጣች ነው፡፡በአለም ካለው ይልቅ በእኛ ያለው እጅግ ታላቅ ነውና ለሰይጣን ፈፅሞ ስፍራ አንሰጠውም፡፡እናም በአለም ዙሪያ ያሉ ክርስቲያኖች ሰይጣን በቤተ ክርስቲያን ላይ የሚያሳድረውን የከፋት እቅድና እንቅስቃሴ ንቁ በመሆን ያለማቋረጥ ያከሽፋሉ፣በኢየሱስ ስም፡፡አሜን፡፡

## ለተጨማሪ ጥናት:

ኦሪት ዘጸአት 19:5; ቲቶ 2:14; 1 ኛ ጴጥሮስ 2:9 AMPC

**የአንድ ዓመት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት**

2 ኛ ቆሮንጦስ 5:1-6:1-2 & መጽሀፈ ምሳሌ 18-19

**የሁለት ዓመት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት**

1 ኛ ተሰሎንቄ 5:12-28 & ትንቢተ ኤርምያስ 24

Leave comments on today's devotional at
*www.rhapsodyofrealities.org*



ሰኞ **7**

# የቤተ ክርስቲያን መነጠቅ ከመቼውም ጊዜ በላይ ቀርቧል

ከዚያም በኋላ እኛ ሕያዋን ሆነን የምንቀረው፥ ጌታን በአየር ለመቀበል ከእነርሱ ጋር በደመና እንነጠቃለን፤ እንዲሁም ሁልጊዜ ከጌታ ጋር እንሆናለን ።
(1ኛ ተሰሎንቄ 4:17)

ሐዋሪያው ጳውሎስ በመንፈስ ስለ ቤተ ክርስቲያን መነጠቅ መገለጥ አግኝቶ እንዲህ አለ “እነሆ፥ አንድ ምሥጢር እነግራችኋለሁ. . .” (1ኛ ቆሮንቶስ 15:51)። ብዙዎች የቤተ ክርስቲያንን መነጠቅ የማይረዱት ለዚህ ነው ፤ ይህ ሚስጥርም መለኮታዊ መገለጥም ነው። እንዲህ አለ “እነሆ፥ አንድ ምሥጢር እነግራችኋለሁ፤ ሁላችን አናንቀላፋም ነገር ግን የኋለኛው መለከት ሲነፋ ሁላችን በድንገት በቅጽበተ ዓይን እንለወጣለን፤ መለከት ይነፋልና ሙታንም የማይበሰብሱ ሆነው ይነሣሉ እኛም እንለወጣለን” (1ኛ ቆሮንቶስ 15:51-52)።

ከላይ የተሰመረበት ክፍል የቤተ ክርስቲያን መነጠቅ በምን ያህል ፍጥነት እንደሚሆን ያሳየናል፤ እጅግ ፈጣን ከመሆኑ የተነሳ ላልተዘጋጁ ሰዎች ምንም አይነት ጊዜ አይኖራቸውም፣ ምክንያቱም ሕይወታችሁን ሁሉ ልትዘጋጁበት የሚገባ ነገር ነው።

በመክፈቻ ጥቅሳችን ላይ “መነጠቅ” ለሚለው ቃል ተመሳሳይ ቃል እናገኛለን፤ ይህም “ሀርፓዞ” ከሚለው የግሪክ ቃል የመጣ ሲሆን “ወደ ላይ ተንሳፎ መነሳት” ማለት ነው፡፡ ትርጉሙም መያዝ፥ ወደላይ ርቆ መነሳት፥ መሳብ፥ መንተት፥ በኃይል መውሰድ ማለት ነው።

የቤተክርስቲያን መነጠቅ በሚሆንበት ጊዜ፣ ያላችሁበት ስፍራ የትም ቢሆን ግድ አይልም፤ የእግዚአብሔር ኃይል ከዚህ ዓለም ነጥቆ ያወጣችኋል። የሞቱ ክርስቲያኖች ይነሳሉ፣ እኛም ከእነርሱ ጋር ጌታን በደመና ላይ እንገናኘዋለን። አቤት ያ ምን አይነት ቀን ነው!

ይህ የሚሆነው መቼ ነው? ከመቼውም በላይ ቀርቧል፤ በቅርብ ባለ ማንኛውም ጊዜ ይሆናል። የእናንተ ኃላፊነት በየቀኑ ሕይወታችሁን ለጌታ

በመኖር መዘጋጀት ነው። በፍቅር መመላለሳችሁን ቀጥሉ እናም እምነታችሁ ጌታ ሲመጣ ከጌታ ጋር ለመሆንና ለመነጠቅ የተነቃቃ ይሁን።

መጽሐፍ ቅዱስ ሲናገር እርሱ እድፈት፥ የፊት መጨማደድ፥ ነውር ወይም እንዲህ ያለ ነገር ወደሌለባት ቤተክርስቲያን ይመጣል ይላል (ኤፌሶን 5:27)። እያንዳንዱን ቀን፥ የሕይወታችሁን እያንዳንዱን ሰዓት የጽድቅን ስራ እየሰራችሁ እና የጽድቅ ፍሬ እያፈራችሁ በእርሱ ጽድቅ ኑሩ።

## የእምነት አዋጅ

ጌታ ኢየሱስ እድፈት፥ የፊት መጨማደድ፥ ነውር ወይም እንዲህ ያለ ነገር ወደሌለባት ቤተክርስቲያን ይመጣል እናም እኔ ዝግጁ ነኝ። እምነቴ በመነጠቅ ለዘላለም ከጌታ ጋር ለመሆን ተነቃቅቷል! ነገር ግን ይህንን አስደናቂ “መነጠቅ” በመጠባበቅ፣ ሕይወቴ እና መሻቴ ስለ እርሱ መንግስት እና የመንግስቱ መስፋት ነው፤ እናም በእኔ አማካኝነት ብዙዎች ለመነጠቅ ይዘጋጃሉ፥ በኢየሱስ ስም። አሜን።

### ለተጨማሪ ጥናት:

1 ኛ ተሰሎንቄ 4:16-17; 1 የዮሐንስ ወንጌል 2:28; የማቴዎስ ወንጌል 24:27

**የአንድ ዓመት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት**

2 ኛ ቆሮንጦስ 6:3-7:1 & መጽሀፈ ምሳሌ 20-21

**የሁለት ዓመት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት**

2 ኛ ተሰሎንቄ 1:1-12 & ትንቢተ ኤርምያስ 25

**Leave comments on today’s devotional at**
***www.rhapsodyofrealities.org***

# ማስ ወሻ

# ማስ ወሻ





# እኛ በምድር ላይ እንግዶች ነን

> ከዓለምስ ብትሆኑ ዓለም የራሱ የሆነውን ይወድ ነበር፤ ነገር ግን እኔ ከዓለም መረጥኋችሁ እንጂ ከዓለም ስለ አይደላችሁ ስለዚህ ዓለም ይጠላችኋል። (ዮሐንስ 15:19)

በአስቴር ዘመን አይሁዳውያን ምርኮኛ በነበሩበት በባዕድ ምድር ላይ ተመቻችተው ተቀምጠው ነበር። በመንግስቱ ውስጥ ኃያል የሆነ ነገር ግን መጥፎ (እንዲሁም የንጉሱ ጓደኛ) የሆነው ሐማን ሊያጠፋቸው እስከሚፈልግበት ጊዜ ድረስ በምድሪቷ ላይ ነጻነትን ተለማምደው ነበር።

የሐማን ጥላቻ እና አይሁዳውያንን የማጥፋት ጥያቄ ምንም ያላወቀችው ንግሥቲቷ አስቴር ከአጎቷ ከመርደክዮስ የሐማንን ሴራ የሚገልጽ ልብ የሚነካ ጥያቄ ደረሳት። በፍጥነት ጣልቃ በመግባት በምድሪቷ ሁሉ ላይ ጸሎት እና ፆም ጠራች (አስቴር 4:16) ። በእርግጥ እግዚአብሔር ጸሎታቸውን ሰምቶ ከሐማን ክፉ እጅ አዳናቸው።

አንዳንድ ጊዜ በምድር ላይ ያለውን ነጻነት ከመለማመዳችሁ የተነሳ፣ በ"እንግዳ ምድር" እንዳላችሁ ወይም በምድር ላይ ለጊዜው ተጓዦች እንደሆናችሁ ትረሱታላችሁ። ይህ በብዙዎች ላይ ሆኗል፥ ከመድረሻው በላይ በጉዞው ላይ አተኩረዋል። አንዳንድ ክርስቲያኖች በራሳቸው ላይ ብቻ በመጠመድ፣ በዚህ ዓለም ነገሮች ተይዘው፣ ትኩረታቸውን አጥተው ሸሽተዋል። ግን ኢየሱስ እንዲህ አለ "ሰው ዓለምን ሁሉ ቢያተርፍ ነፍሱንም ቢያጐድል ምን ይጠቅመዋል" (ማርቆስ 8:36)።

ልባችሁ በጌታ ላይ ይሁን፤ የመንግስቱን ዋና ጉዳዮች እንድትሰሩ ያነቃቃችሁ። ነብሳትን አድኑ። ኢየሱስ እንደተናገረ ትጉና ጸልዩ። ወንጌል በሀገራችሁ በነጻነት እንዲሰራጭ እና እንዲሰፋ ጸልዩ።

ከዓመታት በፊት ወንጌል የተስፋፋባቸው ሀገራት ነበሩ፤ ነገር ግን ዛሬ እነዚሁ ሀገራት ክርስቲያኖችን በብዙ ስደት ወስጥ በማስገባት ወንጌል መስበክን ይከለክላሉ። ምን ተከስቶ ነው? መልሱ ቀላል ነው፤ በእነዚህ ሀገራት ያሉ ክርስቲያኖች ኢየሱስ አድርጉ እንዳለ አላደረጉም፣ "ትጉና ጸልዩ . . ." (ማቴዎስ 26:41)።

ዓላማችንን፣ እዚህ ያለንበትን ምክንያት እና የምንቆየውም ለተወሰነ ጊዜ መሆኑን ማስታወስ አለብን። እኛ በምድር ላይ ላሉ ነብሳት መዳን ከሰማያዊ መንግስት የተላክን የእግዚአብሔር አምባሳደሮች ነን። ስለዚህ መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚናገር "እንግዲህ ከክርስቶስ ጋር ከተነሣችሁ፥ ክርስቶስ በእግዚአብሔር ቀኝ ተቀምጦ ባለበት በላይ ያለውን እሹ። በላይ ያለውን አስቡ እንጂ በምድር ያለውን አይደለም" (ቆላስይስ 3: 1-2)።

## የእምነት አዋጅ

እኔ ከላይ ነኝ ይህንንም በሚገባ አውቃለሁ። በዓለም ዙሪያ የአገልግሎት በሮች ተከፍተዋል እንዲሁም የክርስቶስን ወንጌል ያለመከልከል በኃይል እና በውጤታማነት እንዲያውጁ ለእግዚአብሔር ልጆች ቃል ተሰጥቷቸዋል።

## ለተጨማሪ ጥናት:

የሐዋርያት ስራ 26:16; ቆላስያስ 4:2-4; ዕብራውያን 11:13

የአንድ ዓመት የመጽሐፍ ቅዱስ  ጥናት

2 ኛ ቆሮንጦስ 7:2-16 & መጽሀፈ ምሳሌ 22-23

የሁለት ዓመት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት

2 ኛ ተሰሎንቄ 2:1-10 & ትንቢተ  ኤርምያስ 26

**Leave comments on today's devotional at**
***www.rhapsodyofrealities.org***





# ከሐሰተኛ አስተማሪዎች ተጠበቁ

ነገር ግን ሐሰተኞች ነቢያት ደግሞ በሕዝቡ መካከል ነበሩ እንዲሁም በመካከላችሁ ደግሞ ሐሰተኞች አስተማሪዎች ይሆናሉ፤ እነርሱም የዋጃቸውን ጌታ እንኳ ክደው የሚፈጥንን ጥፋት በራሳቸው ላይ እየሳቡ የሚያጠፋ ኑፋቄን አሹልከው ያገባሉ ። (2ኛ ጴጥሮስ 2:1)

በእግዚአብሔር ቤት ውስጥ ችግር የሚፈጥሩ ሐሰተኛ ወንድሞች እና ነቢያቶች እንዳሉ ሐሰተኛ አስተማሪዎችም አሉ። እነዚህ ለማስተማር ሳይጠሩ ለእራሳቸው የማስተማር አገልግሎትን የሚወስዱ እንዲሁም እራሳቸውን ለአጋንንት በማጋለጥ የሐሰተኛ ትምህርትን የሚያስፋፉ ናቸው። ብዙውን ጊዜ በስህተት መንፈስ በመመራት ሐሰትን ያስተምራሉ።

ለምሳሌ አንዳንድ ሐሰተኛ አስተማሪዎች የክርስቶስ ዳግም መምጣት አስቀድሞ ሆኗል በማለት አስተምረው ብዙዎች እንዲስቱ አድርገዋል። አንዳንዶች ደግሞ የመንፈስ ቅዱስ አጋልግሎት በሐዋሪያት ጊዜ አብቅቷል ይላሉ። አንዳንዶች በህልም ትርጓሜ በመመስረት እንዴት የመኝታ ሁኔታ ህልማቸው ላይ ተጽዕኖ እንደሚያደርግ ይናገራሉ፣ እንዲሁም ምግብ መመገብ በህልም ላይ የሚያስከትለውን ውጤት ያስተምራሉ።

አንዳንዶች እንዲያውም ለችግራችሁ ምክንያት ዘመዶቻችሁ ናቸው እያሉ እስከመናገር ይደርሳሉ፣ እናም በቤተዘመዶች መካካል ጠብን ይፈጥራሉ። ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስ መጋደላችን ከስጋ እና ከደም አይደለም ይላል (ኤፌሶን 6:12)። በሚያሳዝን ሁኔታ አንዳንዶች በእንደነዚህ ዓይነት የሐሰት ትምህርቶች ተታለዋል።

ይህም ሁኔታ ኢየሱስ እንዲህ ብሎ የተናገረውን ያስታውሰናል፡- “መጻሕፍትንና የእግዚአብሔርን ኃይል አታውቁምና ትስታላችሁ” (ማቴዎስ 22:29) ። ቃሉን ለእራሳችሁ እወቁ እናም ማንም አያስታችሁም። የመጽሐፍ

ቅዱስ ቃልን ማጥናት የሕይወታችሁ ቅድሚያ ነገር አድርጉት። መንፈስ ቅዱስ ልባችሁን ለእርሱ እውነት እና ፍቃድ ይከፍታል እናም ሁሉንም ነገር መፈተን ትችላላችሁ (1ኛ ተሰሎንቄ 5:21) ፤ እያንዳንዱን መንፈስ መርምሩ (1ኛ ዮሐንስ 4:1) እናም የእውነትን ቃል በቅንነት ትናገራላችሁ (2ኛ ጢሞቴዎስ 2:15)።

## ጸሎት

ውድ አባት ሆይ፣ በሕይወት መንገዴ ስለምመራበት ቃልህ አመሰግንሃለሁ። ገደብ ለሌለው ብቃት እና የማያልቅ ዕድሎች ላሉበት ሕይወት ዋስትና ለሆነኝ ለአንተ መንፈስ ራሴን አስገዝቻለሁ። እኔ የእግዚአብሔር ልጅ ስለሆንኩኝ ሊታለል አልችልም። በሕይወቴ ያለውን የአንተን ዓላማ እየፈጸምኩ ነው ምክንያቱም ብርሃን እና ደህንነት የሆነኝን ቃልህን አውቃለሁ፤ በኢየሱስ ስም፡፡ አሜን።

## ለተጨማሪ ጥናት:

2 ኛ ጴጥሮስ 2:3 MSG; 1 ኛ ጢሞቴዎስ 4:1-2

**የአንድ ዓመት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት**

2 ኛ ቆሮንጦስ 8-9 & መጽሀፈ ምሳሌ 24-26

**የሁለት ዓመት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት**

2 ኛ ተሰሎንቄ 2:11-17 & ትንቢተ ኤርምያስ 27

**Leave comments on today's devotional at**
***www.rhapsodyofrealities.org***



ሐሙስ 10

# በስማቸው እዘዟቸው

> ኢየሱስም ሕዝቡ እንደ ገና ሲራወጥ አይቶ ርኵሱን መንፈስ ገሠጸና። አንተ ዲዳ ደንቆሮም መንፈስ፥ እኔ አዝሃለሁ፥ ከእርሱ ውጣ እንግዲህም አትግባበት አለ ። (ማርቆስ 9:25)

እንዴት አጋንንትን ማስወጣት እንደምትችሉ ማወቅ የምትፈልጉ ከሆነ ኢየሱስ ከላይ ባለው ጥቅስ ላይ በግልጽ አሳይቷል። ለሁኔታው ተጠያቂ የሆነውን መንፈስ በስሙ ጠርቶ ተናገረው። እንዲህ አለ “አንተ ዲዳ ደንቆሮም መንፈስ፥ እኔ አዝሃለሁ፥ ከእርሱ ውጣ እንግዲህም አትግባበት አለው”። “አንተን እገሥጽሃለሁ” ብቻ አይደለም ያለው። እንደዛ አይደለም፥ የሚገሥጽ አንድ ልዩ ነገር ነበረ። ያንንም አጋንንት በስሙ ጠርቶ፣ አንተ ዲዳ ደንቆሮም መንፈስ በማለት ተናገረው። በእርግጥም አጋንንቱ ወጣ።

“ሰይጣን አስርሃለሁ” ማለት ብቻ በቂ አይደለም። ሰይጣን የዲያቢሎስ አጠቃላይ ስም ነው። በዚያው ጊዜ የምትቃወሙት ዲያቢሎስ ወይም አጋንንት ማን ነው? በጉዳቱ፥ በችግሩ ዓይነት ወይም መንፈስ ቅዱስ በሚገልጥላችሁ መሰረት ልታውቁ ትችላላችሁ። ስራቸውን በሚሰሩበት ጊዜ፣ አጋንንት የማንነታቸውን ባህሪ ይገልጣሉ እናም ይህ እንድታውቋቸው እና በትትክለኛው መንገድ እንድታዟቸው ይረዳችኋል። በተገለጠው የዲያቢሎስ ባህሪ ስሙን ልታውቁ ትችላላችሁ ፤ምክንያቱም ስም የባህሪ መገለጫ ነው። በመጸሐፍ ቅዱስ እንደሚታየው የአጋንንቶች ስም የተሰየመው በባህሪያቸው ነው።

ለምሳሌ ርኩስ መንፈስን ከለያችሁ ይህ ርኩስ መንፈስ ስሙ ማን እንደሆነ ለማወቅ መቸገር የለባችሁም። በዚያው ስም በመጥራት “አንተ ርኩስ መንፈስ በኢየሱስ ስም እንድትወጣ አዝሃለሁ!” ትላላችሁ። ማንኛውም ሰይጣን በኢየሱስ ስም ስታዙት ሊቋቋም አይችልም።

መጽሐፍ ቅዱስ ሲናገር “ . . . በሰማይና በምድር ከምድርም በታች

ያሉት ሁሉ በኢየሱስ ስም ይንበረከኩ ዘንድ” (ፊልጵስዮስ 2:10)። ማርቆስ 6:7 እርኩሳን መናፍስትን እንድናስወጣ ስልጣን እንደተሰጠን ይናገራል። በማቴዎስ 10:8 ላይ “ድውዮችን ፈውሱ፤ ሙታንን አስነሡ፤ ለምጻሞችን አንጹ፤ አጋንንትን አውጡ” ሲል በአጽንዖት ነበር። ሃሌሉያ!

## ጸሎት

ውድ አባት ሆይ፣ አጋንንትን ለማስወጣት በሁሉ ላይ ኃይል ባለው በኢየሱስ ስም እንድጠቀም ስልጣን ስለተሰጠኝ አመሰግናለሁ። ሰይጣን በሕይወቴ፥ በቤቴ ወይም በምወዳቸው ሕይወት ውስጥ ስፍራ የለውም። በማያቋርጥ ድል እመላለሳለሁ፤ በኢየሱስ ስም። አሜን።

## ለተጨማሪ ጥናት:

የማርቆስ ወንጌል 1:25-26; የማርቆስ ወንጌል 16:17; የሉቃስ ወንጌል 10:18-19

**የአንድ ዓመት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት**

2 ኛ ቆሮንጦስ 10:1-18 & መጽሀፈ ምሳሌ 27-28

**የሁለት ዓመት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት**

2 ኛ ተሰሎንቄ 3:1-10 & ትንቢተ ኤርምያስ 28

**Leave comments on today’s devotional at**
***www.rhapsodyofrealities.org***



## አርብ 11

# የእርሱን በጎነት እና ልቀት ማሳየት

> እናንተ ግን ከጨለማ ወደሚደነቅ ብርሃኑ የጠራችሁን የእርሱን በጎነት እና ፍጽምና እንድትናገሩ የተመረጠ ትውልድ፥ የንጉሥ ካህናት፥ ቅዱስ ሕዝብ፥ ለርስቱ የተለየ ወገን [ለእግዚአብሔር የተለያችሁ] ናችሁ ።
> (1ኛ ጴጥሮስ 2:9 የአምፕሊፋይድ ትርጉም)

እንደ እግዚአብሔር ልጆች የክርስቶስን በጎነት እና ፍጽምና እንድናሳይ ተጠርተናል፤ ይህ አገልግሎታችህን ሕይወታችንም ጭምር ነው። ኢየሱስ እንዲህ አለ “እኔ የወይን ግንድ ነኝ እናንተም ቅርንጫፎች ናችሁ . . .” (ዮሐንስ 15:5) ። ቅርንጫፎች ፍሬ የሚያፈራው የወይኑ ግንድ አካል ናቸው። የእርሱን ፍሬ፣ በጎነትን እናፈራለን።

ጥላቻ፥ ምሬት፥ ንዴት፥ ውሸት እና የመሳሰሉት የእግዚአብሔር በጎነት መገለጫ አይደሉም። ስለዚህ እነዚህ ዳግም የተፈጠረው መንፈሳችሁ ባህሪ ወይም መገለጫዎች አይደሉም። ይልቁኑ የእግዚአብሔርን ደግነት፥ ፍቅር፥ ርህራሄ፥ ትዕግሥት፥ ገርነት፥ ቸርነት፥ ጥበብ እና ልቀት ማሳየት አለባችሁ። ስለዚህ በቤታችሁ፥ በትምህርት ቤት ወይም በሥራ ቦታ እና በየትኛውም ስፍራ ልቀትን አሳዩ። በእናንተ በሆነ ነገር ሁሉ ላይ ይታይ።

በተጨማሪም ንግግራችሁ ጸጋን እና እውነትን የሚያስተላልፍ መሆን አለበት። ቸር፣ በሚያበረታቱ እና እምነትን በሚያነቃቁ፣ ሕይወት እና ኃይል በተሞሉ ቃላት ነብሳትን እያዳናችሁ፣ የእርሱን በጎነት እና ልቀት አሳዩ።

በዚህ ዓለም አስደናቂ አድርጎናል፤ የእርሱን ክብር እና ጽድቅ የሚገልጥ አድርጎናል። በእናንተ በኩል በሰዎች ልብ ውስጥ መንግሥቱን እያጸና፣ ፍቅሩን ለሌሎች ይገልጣል። ሃሌሉያ!

## የእምነት አዋጅ

የክብር፥ የኃይል፥ የስኬት እና ተጽዕኖ የሚፈጥር ሕይወት እኖራለሁ። የእርሱን ድንቅ ስራ፥ በጎነት፥ ፍጽምና፥ ልቀት እና ጥበብ እንዳሳይ በክርስቶስ ኢየሱስ የእርሱ የእጅ ስራ ነኝ፤ በኢየሱስ ስም፡፡ አሜን።

## ለተጨማሪ ጥናት:

ኤፌሶን 2:10; የማቴዎስ ወንጌል 5:14-16

### የአንድ ዓመት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት

2 ኛ ቆሮንጦስ 11:1-15 & መጽሀፈ ምሳሌ 29-31

### የሁለት ዓመት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት

2 ኛ ተሰሎንቄ 3:11-18 & ትንቢተ ኤርምያስ 29

**Leave comments on today’s devotional at**
***www.rhapsodyofrealities.org***



## ቅዳሜ 12

# የእርሱን ራእይ በመፈጸም ላይ ትኩረት አድርጉ

> ዓለምን ወይም በዓለም ያሉትን አትውደዱ፤ በዓለም ያለው ሁሉ እርሱም የሥጋ ምኞትና የዓይን አምሮት ስለ ገንዘብም መመካት ከዓለም ስለ ሆነ እንጂ ከአባት ስላልሆነ፥ ማንም ዓለምን ቢወድ የአባት ፍቅር በእርሱ ውስጥ የለም ። (1ኛ ዮሐንስ 2:15-16)

የጌታ መምጣት ከመቼውም ይልቅ ቅርብ መሆኑ አያጠራጥርም። ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፤ “. . . ክህደቱ አስቀድሞ ሳይመጣና የዓመፅ ሰው እርሱም የጥፋት ልጅ ሳይገለጥ፥ አይደርስምና” (2ኛ ተሰሎንቄ 2:3)። የአምፐሊፋይድ ክላሲክ ትርጉም እንዲህ ብሎ ያስቀምጠዋል፤ “ክህደቱ አስቀድሞ ሳይመጣ [በዚያን ጊዜ ክርስቲያን ነን ብለው የሚያስመስሉ ሰዎች ታላቅ ውድቀት ሳይሆን] እና የጥፋት ልጅ የሆነው የዓመፅ (የኃጢያት) ልጅ ሳይገለጥ ያ ቀን አይመጣም።”

ይህ ማለት ክርስቲያን ነን የሚሉ ነገር ግን ከእምነታቸው የሚወድቁ ሰዎች አሉ ማለት ነው፤ ይህም ሰዎች በኢየሱስ ላይ ያላቸውን እምነት በመተው በፍቃዳቸው ይክዳሉ ማለት ነው። ይህ አሁንም እየሆነ ነው፤ ዋነኛው ምክንያትም የዚህ ዓለም አሳብ፥ የባለጠግነት መታለል እና ሌሎች ነገሮችን በመመኘት ነው። ስለዚህ እግዚአብሔር የሚፈልገው ምንድን ነው፥ በእነዚህ የመጨረሻ ቀናትን መመላለስ ያለባችሁስ እንዴት ነው? ምን አይነት ምርጫዎችን ታደርጋላችሁ?

የእርሱ ምክር በመከፈቻ ጥቅሳችን ላይ እንዳነበብነው ነው። ትኩረታችሁ በክርስቶስ ላይ አድርጉ! ትኩረታችሁ በዚህ ዓለም ጊዜያዊ ደስታ ላይ ሳይሆን በመንግስቱ ላይ ይሁን። ቆላስይስ 3:1 በተዋበ ሁኔታ ይገልጸዋል። እንዲህ ይላል “እንግዲህ ከክርስቶስ ጋር ከተነሣችሁ፥ ክርስቶስ በእግዚአብሔር ቀኝ ተቀምጦ ባለበት በላይ ያለውን እሹ።”

ድካማችሁን ሁሉ፣ የእግዚአብሔርን ህልም ማለትም መንግስቱን የማስፋት እና ወንጌልን ለዓለም የማሰራጨት ራእዩ ላይ አውሉ። በዚህ

ዓለም ነገር ላይ ከተጣበቁት እና ስለሚያገኙት እና ስለ እራሳቸው ምኞት ብቻ ከሚያስቡ መካከል መሆንን እንቢ በሉ። እነርሱ በዚህ ዓለም መንፈስ ተሸንፈዋል። ኢየሱስ እንዲህ አለ “ሰው ዓለምን ሁሉ ቢያተርፍ ነፍሱንም ቢያጐድል ምን ይጠቅመዋል?” (ማርቆስ 8:36)። በክርስቶስ ላይ የተመሰረተ፥ ሥር የሰደደ እና የቆመ ሕይወት መኖራችሁ በጣም አስፈላጊ ነው። የጌታን ሥራ በደስታ በመስራት ጸንታችሁ፥ ሳትናወጡ ቁሙ። ሃሌሉያ!

## የእምነት አዋጅ

ውድ አባት ሆይ፥ በቅዱስ ጥሪ ስለጠራኸኝ እና ለአንተ እንድኖር የውስጥ ጥንካሬ ስለሰጠኸኝ አመሰግንሃለሁ። እኔ በክርስቶስ ኢየሱስ ሥር ሰድጄ ተመስርቻለሁ፤ ሥጋን ከክፉ መሻቱና ከምኞቱ ጋር ሰቅዬዋለሁ። የእኔ ብቸኛ መሻት የአንተን መንግስት ማስፋት፥ የክርስቶስን ፍቅር እና የእርሱን ማዳን ለዓለም ሁሉ ማሳየት ነው። ሃሌሉያ!

## ለተጨማሪ ጥናት:

የዮሐንስ ራዕይ 3:11-13

| የአንድ ዓመት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት |
| --- |
| 2 ኛ ቆሮንጦስ 11:16-33 & መጽሀፈ መክብብ 1-2 |

| የሁለት ዓመት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት |
| --- |
| 1 ኛ ጢሞቴዎስ 1:1-7 & ትንቢተ ኤርምያስ 30 |

**Leave comments on today’s devotional at**
***www.rhapsodyofrealities.org***



## እሁድ 13

# በእርሱ ፍጹም እና ሙሉ መሆን

> ከእናንተ የሆነ የክርስቶስ ባሪያ ኤጳፍራ ሰላምታ ያቀርብላችኋል፤ በእግዚአብሔር ፈቃድ ሁሉ ተረድታችሁና ፍጹማን ሆናችሁ እንድትቆሙ፥ ሁልጊዜ ስለ እናንተ በጸሎቱ ይጋደላል ።
> (ቆላስይስ 4፡12)

ከላይ ባለው ጥቅስ “ፍጹም” እና “ሙሉ” የሚሉት ቃላት አንዱ ሌላውን ሊተካው ይችላል፡፡ በሌላ አነጋገር “ፍጹም” በሚለው ቃል ምትክ “ሙሉ” ፤ “ሙሉ” በሚለውም ምትክ “ፍጹም” የሚለውን መተካት ይቻላል፡፡

እዚህ ላይ “ፍጹም” የሚለው ቃል መጽናትን አለመናወጥን ያመለክታል፡፡ መብሰልን ወይንም “ሙሉ በሙሉ ማደግንም” ሊያመለክት ይችላል፡፡ የሙሉነት ቦታ ነው፣ የማስተዋልን፣ የጥበብን እና የእውቀትን፣ የመንፈስን ሙሉነት ያመለክታል፡፡ ሃሌሉያ!

ስለሆነም ኤጳፍራ በመንፈስ ለቆላስይስ ክርስቲያኖች ጸንተው በመቆም በክርስቶስ ሙሉና ፍጹም ሆነው ወደዚህ ሙላት እንዲመጡ እየጸለየ ነበር። በክርስቶስ ፍጹም እና ሙሉ እንዲሆኑ፡፡ እግዚሃብሄር በህይወታችሁ ይህ እንዲሆን ይፈልጋል፡፡ በሙላት ያደገ ክርስቲያን እንድትሆኑ ይፈልጋል፣ የእግዚሃብሄርን ነገሮች ለማድረግ ሙሉ በሙሉ ያደገና የበሰለ ክርስቲያኖች እንድትሆኑ ይፈልጋል፡፡

የበለጠ መንፈሳዊ ብስለት ሲኖራችሁ፣ በበለጠ እግዚሃብሄር ለህይወታችሁ ያለውን ህልም ለመፈጸም ትችላላችሁ፡፡ ስለሆነም ለራሳችሁ መንፈሳዊ እድገት ግብን አስቀምጡ፡፡ ለራሳችሁ እንዲህ በሉ፣ “የበለጠ አድጋለሁ፣ መንፈሳዊ የሆኑ ነገሮችን ብቻ ወደማስብበት፣ በበሰለ ሁኔታ ስለክርስቶስ ወደማስብበት፣ በእግዚሃብሄር ቃል ሙሉ ወደምሆንበት የብስለት ስፍራ እየደረስኩኝ፣ ያንንም ለመፈጸም እየገሰገስኩኝ ነው፡፡”

ኤፌሶን 4፡12-13 እግዚሃብሄር የአገልግሎት ስጦታዎችን ለቤተ-

ክርስቲያን በሚከተለው ዓላማ እንደሰጠ ይነግረናል፡- “ሁላችን የእግዚአብሔርን ልጅ በማመንና በማወቅ ወደሚገኝ አንድነት፥ ሙሉ ሰውም ወደ መሆን፥ የክርስቶስም ሙላቱ ወደሚሆን ወደ ሙላቱ ልክ እስክንደርስ ድረስ፥ ቅዱሳን አገልግሎትን ለመሥራትና ለክርስቶስ አካል ሕንጻ ፍጹማን ይሆኑ ዘንድ።”

ወደ ክርስቶስ ፍጹም ሙላት ልክ መድረስ የማይቻል ነገር ቢሆን ኖሮ፣ እግዚሃብሄር አድርጉ አይለንም ነበር፡፡ ይህ የእርሱ ራእይ ነው፡፡ ስለሆነም በትጋት ቃሉን እያጠናችሁ እና እያሰላሰላችሁ፣ ራሳችሁን ለመንፈስ ቅዱስ አገልግሎት በማስገዛት ፈጽሙት፡፡

## የእምነት አዋጅ

በክርስቶስ የእግዚሃብሄር ሙላት በስጋ ተገልጧል፣ እኔ ደግሞ የኃይላት እና የስልጣናት የበላይ በሆነው በእርሱ ሙሉ ነኝ፣ ያለማቋረጥ በቃሉ ብርሃን እውቀት ስመላለስ፣ ተረጋግቼ ሳልናወጥ በእምነት ጸንቼ፣ በክርስቶስ የከፍታ ህይወትን እኖራለሁ፡፡

### ለተጨማሪ ጥናት:

ኤፌሶን 4:14-15; ዕብራውያን 5:14

የአንድ ዓመት የመጽሐፍ ቅዱስ  ጥናት

2 ኛ ቆሮንጦስ 12:1-21 & መጽሀፈ መክብብ 3-5

የሁለት ዓመት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት

1 ኛ ጢሞቴዎስ 1:8-14 & ትንቢተ  ኤርምያስ 31

**Leave comments on today’s devotional at**
***www.rhapsodyofrealities.org***




## ሰኞ 14

# ልባችሁን ይፈልገዋል

> ልጄ ሆይ፥ ልብህን ስጠኝ፥ ዓይኖችህም መንገዴን ይውደዱ ። (ምሳሌ 23፡26)

የሉበት ሁኔታ ምንም የተለያየ ቢሆንም፣ ሰዎች ሁሉ ተመሳሳይ ናቸው፡፡ ይህም ማለት ለምሳሌ በልባቸው ለውጥ እስካልመጣ ድረስ፣ ድሃም ሃብታምም ሰዎች ተመሳሳይ ናቸው፡፡ አንድ ሰው ድሃም ክፉም ከሆነ፣ ሃብታም ቢሆንም የተለየ አይሆንም፡፡ ድሃ እያለ በልቡ ውስጥ ያለውን ክፋት የሚያስፈጽምበት ንብረት ወይም ገንዘብ አልነበረውም። ስለሆነም ሃብታም ሲሆን፣ ባለው ንብረት በልቡ ውስጥ ያለውን ክፋት ለመፈጸም ይችላል፡፡

ገንዘብ ባህሪን አጉልቶ ያወጣል፡፡ ባላቸው ሃብት መጠን፣ ሰዎች በውስጣቸው ያለውን መልካምነት ወይንም ክፋት ያስፈጽማሉ፡፡ ኢየሱስ እንዲህ አለ፣ "ዛፍ ከፍሬዋ ትታወቃለችና ዛፍዋን መልካም፥ ፍሬዋንም መልካም አድርጉ፥ ወይም ዛፍዋን ክፉ ፍሬዋንም ክፉ አድርጉ" (ማቴዎስ 12፡33)፡፡ ይህም ማለት ሰዎች በውስጣቸው ካለው ማንነት የተለዩ ሊሆኑ አይችሉም፡፡ ስለሆነም እግዚሃብሄር የሚፈልገው ምንድን ነው? እርሱ የሚፈልገው በልባችሁ ውስጥ ለውጥ ማለትም የውስጥ መቀየር እንዲኖራችሁ ነው፡፡

መንግስቱን በመጀመሪያ በልባችሁ ውስጥ የሚመሰርተውም በዚህ ምክንያት ነው፡፡ ፍቅሩን በመጀመሪያ በልባችሁ ውስጥ ያስቀምጣል፡፡ ስራውን መስራት የሚፈልገው በልባችሁ ውስጥ ነው፣ በረከቱ ሁሉ ያለው በልባችሁ ውስጥ ነው፡፡ ከዛም ከልባችሁ ውስጥ ለሌሎች ይፈሳል፡፡ ዳግም ስለተወለዳችሁ የእግዚሃብሄር ህይወት እና ባህሪ በልባችሁ አለ፣ እናም አሁን በክርስቶስ ህይወት ሰጪዎች ናችሁ፡፡

በነፍሳችሁ እና በሰውነታችሁ የተገለጠው ለውጥ እና ክብር በመንፈሳችሁ ያለው የእግዚሃብሄር ህይወት እና ተፈጥሮ ያመጣው ተጽእኖ

እና ውጤት ነው፡፡

የመግቢያ ጥቅሳችን እንዲህ ይላል፣ “ልጄ ሆይ ልብህን ስጠኝ...”። እስካሁን ዳግም ያልተወለዳችሁ ከሆናችሁ፣ የእናንተ ጊዜ አሁን ነው፣ ልባችሁን ስጡት፡፡ የድህነት ገጽ ወዳለበት ገልጣችሁ ጸሎቱን ከልባችሁ ጸልዩ፡፡

## ጸሎት

ውድ አባት ሆይ፣ መንግስትህን በልቤ ውስጥ ስላኖርክ አመሰግንሃለው። በልቤ የወንጌልን እውነታ እና የመንግስታችንን ህይወት አስባለሁ፤ እይዛለሁም፡፡ ወንጌልን ለመቀበል ልባቸው ክፍት እንዲሆን፣ እንዲድኑ፣ ለመዳናቸው የእግዚሃብሄር ኃይል በልባቸው እንዲያድር፣ በአለም ላይ ላሉት ላልዳኑት ሁሉ እጸልያለሁ፤ በኢየሱስ ስም፡፡ አሜን፡፡

## ለተጨማሪ ጥናት:

የሉቃስ ወንጌል 6:45; ዕብራውያን 10:22

የአንድ ዓመት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት

2 ኛ ቆሮንጦስ 13:1-14 & መጽሀፈ መክብብ 6-8

የሁለት ዓመት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት

1 ኛ ጢሞቴዎስ 1:15-20 & ትንቢተ ኤርምያስ 32

**Leave comments on today’s devotional at**
***www.rhapsodyofrealities.org***

# ማስ ወሻ

# ማስ ወሻ



## ማክሰኞ 15

# እርሱ ከእናንተ ጋር እና በእናንተ ውስጥ ነው

> ብትወዱኝ ትእዛዜን ጠብቁ። እኔም አብን እለምናለሁ ለዘላለምም ከእናንተ ጋር እንዲኖር ሌላ አጽናኝ ይሰጣችኋል፤ እርሱም ዓለም የማያየውና የማያውቀው ስለ ሆነ ሊቀበለው የማይቻለው የእውነት መንፈስ ነው፤ ነገር ግን ከእናንተ ዘንድ ስለሚኖር በውሥጣችሁም ስለሚሆን እናንተ ታውቃላችሁ ። (ዮሐንስ 14፡16-17)

ከላይ የተቀመጠው የሚያጽናና እና ነፍስን ከፍ የሚያደርግ ቃል፣ ኢየሱስ ከማረጉ በፊት የተናገረው ንግግር ነው፡፡ ደቀ-መዛሙርቱ እንደሚናፍቁት ያውቃል፤ ስለሆነም እንዲህ አላቸው፡- “አትጨነቁ! ወደ አብ እኼዳለሁ፣ መንፈስ ቅዱስንም (ሌላውን አጽናኝ) እንዲልክላችሁ እጠይቀዋለሁ፡፡ እርሱ ሲመጣ፣ በልባችሁ ውስጥ ይኖራል፣ እኔን መፈለግ አይጠበቅባችሁም ወይንም አለመኖሬ አይሰማችሁም፡፡ በጎዳና ላይ ከእናንተ ጋር ከመራመድ ይልቅ፣ በእናንተ ውስጥ ሆኜ በጎዳናዎች እራመዳለሁ፡፡” ክብር ለእግዚሃብሄር ይሁን!

ኢየሱስ ቃሉን ፈጽሟል እናም በበዓለ ኀምሳ ቀን አብ መንፈስ ቅዱስን ልኳል፡፡ የሐዋሪያት ስራ 2፡1-4 እንዲህ ያውጃል፡- “በዓለ ኀምሳ የተባለውም ቀን በደረሰ ጊዜ፥ ሁሉም በአንድ ልብ ሆነው አብረው ሳሉ፥ ድንገት እንደሚነጥቅ ዓውሎ ነፋስ ከሰማይ ድምፅ መጣ፥ ተቀምጠው የነበሩበትንም ቤት ሁሉ ሞላው። እንደ እሳትም የተከፋፈሉ ልሳኖች ታዩአቸው፤ በያንዳንዳቸውም ላይ ተቀመጡባቸው።በሁሉም መንፈስ ቅዱስ ሞላባቸው፥ መንፈስም ይናገሩ ዘንድ እንደ ሰጣቸው በሌላ ልሳኖች ይናገሩ ጀመር፡፡” አሁን ዳግም ስለተወለዳችሁ፣ ኢየሱስን ማፈላለግ አይጠበቅባችሁም፣ “ጌታ ሆይ ወዴት አለህ?” እያላችሁ መቼም ቢሆን ማልቀስ አይጠበቅባችሁም። አሁን እርሱ እናንተ ውስጥ ነው፡፡ ይህም ማለት የእግዚሃብሄር መገኘት በእናንተ ልብ ውስጥ ነው፡፡

ከአሁን በፊት ስለ እግዚሃብሄር እና ስለክርስትና ያላችሁን አረዳድ አላውቅም፣ ነገር ግን ይህንን እወቁ፣ መንፈስ ቅዱስን ከተቀበላችሁ፣

እግዚሃብሄር በውስጣችሁ ነው፡፡ ዮሐንስ እንዲህ ቢል አያስደንቅም፡- “ልጆች ሆይ፥ እናንተ ከእግዚአብሔር ናችሁ (ጠላቶቻችሁን) አሸንፋችኋቸውማል፥ በዓለም ካለው ይልቅ በእናንተ ያለው ታላቅ ነውና” (1ኛ ዮሐንስ 4፡4)፡፡

በህይወታችሁ ላይ የተጋረጠው ነገር ምንም ቢሆን፣ አዲስ መገለጥ አለ፣ ያም በእናንተ ውስጥ መለኮት መገለጡ ነው! ጳውሎስ እንዲህ ይለዋል፡ - “ይህም ቃል ከዘላለምና ከትውልዶች ጀምሮ ተሰውሮ የነበረ ምሥጢር ነው፥ አሁን ግን ለቅዱሳኑ ተገልጦአል፤ ለእነርሱም እግዚአብሔር በአሕዛብ ዘንድ ያለው የዚህ ምሥጢር ክብር ባለ ጠግነት ምን እንደ ሆነ ሊያስታውቅ ወደደ፥ ምሥጢሩም የክብር ተስፋ ያለው ክርስቶስ በእናንተ ዘንድ መሆኑ ነው” (ቆላስይስ 1፡26-27)።

ይህንን አዳም አያውቀውም ነበር፡፡ አብርሃም አያውቀውም ነበር። ይስሃቅም አያውቀውም ነበር፡፡ ከቀድሞዎቹ አባቶችም ማንም ይህንን ምስጢር አያውቀውም ነበር፡፡ ይህ አማኑኤል (እግዚሃብሄር ከኛ ጋር) ከሚለው ይበልጣል፣ ይህ መንግስተ ሰማያት በእናንተ ውስጥ ማለት ነው! እግዚሃብሄር በሙላቱ በእናንተ ውስጥ ሲኖር፣ በእናንተም በኩል ሲገለጥ ማለት ነው፡፡ እግዚሃብሄር ለዘላለም ይባረክ፡፡

## ጸሎት

ውድ አባት ሆይ፣ ክርስቶስ በመንፈሱ በእኔ ውስጥ እንዲኖር ስላለኝ በረከትና ታላቅ ክብር አመሰግንሃለሁ፣ እርሱ በውስጤ በመኖሩ ምክንያት፣ የእግዚሃብሄርን ፈቃድ ለማከናወን መለኮታዊ በሆነ ኃይል እና ልዕለ-ተፈጥሮአዊ ጥበብ ተሞልቻለሁ፣ የዲያቢሎስን አሳሳች መንገዶችን እና የዚህን አለም የጥፋት ተጽእኖዎችን በማሸነፍ እኖራለሁ፡፡ ሃሌሉያ!

## ለተጨማሪ ጥናት:

የሐዋርያት ስራ 2:1-4; 1 ኛ ቆሮንጦስ 3:16; የሐዋርያት ስራ 17:28

የአንድ ዓመት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት

ገላትያ 1:1-24 & መጽሀፈ መክብብ 9-12

የሁለት ዓመት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት

1 ኛ ጢሞቴዎስ 2:1-15 & ትንቢተ ኤርምያስ 33

**Leave comments on today’s devotional at**
***www.rhapsodyofrealities.org***



## ረቡዕ 16

# ሃሰተኞች ወንድሞች አሉ

> ነገር ግን ባሪያዎች ሊያደርጉን በክርስቶስ ኢየሱስ ያለንን አርነታችንን ይሰልሉ ዘንድ ሾልከው በስውር ስለ ገቡ ስለ ሐሰተኞች ወንድሞች ነበረ ። (ገላቲያ 2፡4)

መጽሐፍ ቅዱስ ስለ እነዚህ ሶስት ስብስቦች ይነግረናል፡- ሐሰተኛ አስተማሪዎች፣ ሐሰተኛ ነብያት እና ሐሰተኛ ወንድሞች ናቸው፡፡ በእነዚህ የመጨረሻ ቀናት ስለሚያደርጉትም የተለያዩ ነገሮች በግልጽ ይነግረናል፡፡ ሐሰተኛ ወንድሞች በቤተ-ክርስቲያን ውስጥ ሊኖሩ ይችላሉ? በእርግጥ ይገኛሉ! ሐሰተኛ ወንድሞች የሚባሉት በእግዚሃብሄር ሰዎች መካከል ሆነው፣ ለኢየሱስ ክርስቶስ ባላቸው ፍቅር የተነሳ ሳይሆን ለተለየ ዓላማ የሚመጡ ናቸው፡፡

የመግቢያ ጥቅሳችን በክርስቶስ ኢየሱስ ያለንን አርነት ለመሰለል ሾልከው እንደሚመጡ እና ባሪያዎች ሊያደርጉን እንደሚጥሩ ይነግረናል። የሆነ ጥቅም ለማግኘት፣ ሐሰተኛ ማንነትን ያሳያሉ፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፡- “ገንዘብንም በመመኘት (በክፉ ምኞት፣ በስግብግብነት) በተፈጠረ ነገር (በማታለያ ቃል) ይረቡባችኋል፤ ፍርዳቸውም ከጥንት ጀምሮ አይዘገይም ጥፋታቸውም አያንቀላፋም” (2ኛ ጴጥሮስ 2፡3 የአምፕሊፋይድ ትርጉም)፡፡

የሐሰት ወንድሞች ሁልጊዜ ከሌሎች ወንድሞች ገንዘብ የማግኛ መንገዶችን ያሰላሉ፡፡ እነርሱ ግን አስራት አይከፍሉም ለቤተ-ክርስቲያንም አይሰጡም፡፡ አላማቸው በወንድሞች መነገድ ነው፡፡ ለገንዘብ ምንም ነገር ያደርጋሉ፡- ፓስተሮቻቸውን፣ መሪዎቻቸውን፣ ቤተ-ክርስቲያንን ጨምሮ ይክዳሉ፡፡ ለገንዘብ ሲሉ፣ የቤተ-ክርስቲያንን ምስጢር ወደ ውጪ የሚያወጡ፣ ወይንም ለባለስልጣናት ወይም ለብዙሃን መገናኛዎች የሚያሳውቁ እነርሱ ናቸው፡፡ በእኛ ላይ በተቃርኖ አንዳች ክስን በማግኘት ተስፋ፣ እኛን ለመሰለል በመካከላችን እንዳሉ መጽሐፍ ቅዱስ ይነግረናል፡፡

አስመሳዮች ስለሆኑ ሐሰተኞች ወንድሞችን መለየት ቀላል ላይሆን ይችላል፡፡ ኢየሱስ ግን እንዲህ ብሏል፡- “ስለዚህም ከፍሬያቸው ታውቋቸዋላችሁ” (ማቴዎስ 7፡20)፡፡ ሐሰተኞች ወንድሞችን አንድ የመለያ

ምልክት ስልጣንን አያከብሩም፡፡ ፓስተሩ ወይንም የቤተ-ክርስቲያን መሪዎች የሚሉትን ለምን ማመን ወይም ማድረግ እንደሌለባቸው ሌሎችን ለማሳመን ጥረት ያደርጋሉ፡፡ ለምሳሌ በግላችሁ የፓስተሩን ምሪት ወይንም እርዳታ እንደምትፈልጉ ከሰሙ፣ በጣም የዋሆች ናችሁ ብለው ያጣጥሉባችኋል፡፡

ሐሰተኞች ወንድሞችን በተመለከተ፣ ለይተን እንድናውቃቸው እና ከሚያመጡት የጥፋት ተጽእኖ የተነሳ፣ ከእነሱ ጋር ግንኙነት እንዳይኖረን እግዚሃብሄር መክሮናል፡፡ ብዙ ክርስቲያኖች ከዚህ ዓይነት ያልተቀደሰ ግንኙነት የተነሳ፣ በእምነታቸው ወድቀዋል፡፡ ስለሆነም ቃሉ የሚላችሁን አድርጉ "ያለ ሥርዓት ከሚሄድ ወንድም (እህትን ጨምሮ) ሁሉ ትለዩ ዘንድ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም እናዛችኋለን" (2ኛ ተሰሎንቄ 3፡6)፡፡

## ጸሎት

ጌታ ሆይ፣ በመንፈስ ቅዱስ የስህተትን መንፈስ በመረዳት በጥበብ ስለምራመድ አመሰግንሃለሁ፡፡ ቃልህ ወደ ትክክለኛው መንገድ እንድራመድ እና ግንኙነቶቼን በተመለከተ ይመራኛል፡፡ ለህይወቴ አንተ ወዳለህ ፍጹም ፍቃድ እና አላማ እመራለሁ፤ በኢየሱስ ስም፡፡ አሜን፡፡

## ለተጨማሪ ጥናት:

2 የዮሐንስ ወንጌል 1:9-10; 2 ኛ ተሰሎንቄ 3:6 AMPC

የአንድ ዓመት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት

ገላትያ 2:1-21 & መኃልየ መኃልይ ዘሰለሞን 1-2

የሁለት ዓመት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት

1 ኛ ጢሞቴዎስ 3:1-7 & ትንቢተ ኤርምያስ 34

**Leave comments on today's devotional at**
***www.rhapsodyofrealities.org***





# ስለእግዚሃብሄር ነገር ትጉህ ሁኑ

> ወደ እግዚአብሔር ቅረቡ ወደ እናንተም ይቀርባል። እናንተ ኃጢአተኞች፥ እጆቻችሁን አንጹ፤ ሁለት አሳብም ያላችሁ እናንተ፥ ልባችሁን አጥሩ። ተጨነቁና እዘኑ አልቅሱም፤ ሳቃችሁ ወደ ኀዘን ደስታችሁም ወደ ትካዜ ይለወጥ ። (ያዕቆብ 4፡8-9)

ኤፌሶን 5፡15-16 በተለይ በመጨረሻው ዘመን ተገቢ የሆነ ተግሳጽ ነው፡- "እንግዲህ እንደ ጥበበኞች እንጂ ጥበብ እንደሌላቸው ሳይሆን እንዴት እንድትመላለሱ በጥንቃቄ ተጠበቁ፤ ቀኖቹ ክፉዎች ናቸውና ዘመኑን ዋጁ።" አደጋው እጅግ ከፍተኛ ነው፡፡ እንደ እግዚሃብሄር ልጅ ህይወታችሁን በቸልተኝነት ልትኖሩ አትችሉም፡፡ እናንተ የኢየሱስ ክርስቶስ ናችሁ፣ ስለሆነም በህይወታችሁ አገልግሉት፡፡ ለእርሱ ኑሩ፡፡

መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፡- "ወይስ ሥጋችሁ ከእግዚአብሔር የተቀበላችሁት በእናንተ የሚኖረው የመንፈስ ቅዱስ ቤተ መቅደስ እንደ ሆነ አታውቁምን? በዋጋ ተገዝታችኋልና ለራሳችሁ አይደላችሁም፤ ስለዚህ በሥጋችሁ እግዚአብሔርን አክብሩ" (1ኛ ቆሮንቶስ 6፡19-20)፡፡ የራሳችሁ አይደላችሁም የኢየሱስ ክርስቶስ ናችሁ፣ በህይወታችሁ እንድትፈጽሙት የሚጠብቅባችሁ አላማ አለው፡፡ በእርሱ ያላችሁን አላማ ማወቅ እና መፈጸም ለእናንተ እጅግ አስፈላጊ ነው፡፡

የህይወት ትርጉም ስለራሳችሁ ግላዊ ህልሞች፣ እቅዶች፣ ፍላጎቶች ወይም ራእዮች ብቻ አይደለም፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፡- "ይህ ሁሉ እንዲህ የሚቀልጥ ከሆነ፥ የእግዚአብሔርን ቀን መምጣት እየጠበቃችሁና እያስቸኰላችሁ፥ በቅዱስ ኑሮ እግዚአብሔርንም በመምሰል እንደ ምን ልትሆኑ ይገባችኋል? ስለዚያ ቀን ሰማያት ተቃጥለው ይቀልጣሉ የሰማይም ፍጥረት በትልቅ ትኩሳት ይፈታል" (2ኛ ጴጥሮስ 3፡11)፡፡ በዚህ ምድር ውስጥ የምታይዋቸው የተዋቡ ህንጻዎች ወይም የሰዎች ምድራዊ ስኬት ምንም ልዩነት አያመጣም፣ ሁሉም ነገር ጠፊ ነው፡፡

በምድር ላይ ለእግዚአብሄር ከመቼውም ጊዜ በበለጠ ውብ የሆነውን

ቤተ-መቅደስ የሰራውን ንጉስ ሰለሞንን ያስታውሰኛል፡፡ እጅግ በጣም ተወድሶ ነበር፣ በእርግጥም እግዚሃብሄር ተደስቶ ባርኮታል፡፡ ነገር ግን የእኛ እግዚሃብሄር በእጅ በተሰራ ቤተ-መቅደስ ውስጥ አይኖርም፡፡ ጣኦትን በማምለክ ባአልን ማገልገል ሲጀምሩ፣ ውብ የሆነው ቤተ-መቅደስ ወደመ፣ በቃሉ መሰረት ካለመሄድ የሚመጣ ቅጣት ነበር፡፡

ስለምድራዊ ነገሮች እግዚአብሄር ግድ አይለውም፡፡ በዚህ ምድር ውስጥ ሊኖራችሁ የሚችለው ነገር ሁሉ፣ የመጣው አስቀድሞ ከነበረ ነገር ነው፤ ይህ እውነት ከሆነ፣ ሁሉን ነገር በመጀመሪያ ለሰራው ህይወታችሁን ለምን አትኖሩም? በህይወታችሁ አገልግሉት፡፡ ትጉህ ሁኑ፤ ጌታን በማገልገል እጅግ የተጋችሁ ሁኑ፡፡

## ጸሎት

ለእግዚሃብሄር ክብር ተወልጃለሁ፣ ከእርሱ ጋር ለመመላለስ እና ለእርሱ ክብር ለማምጣት ተወልጃለሁ፡፡ እርሱን እያስደሰትኩና በመልካም ስራ ሁሉ ፍሬያማ እየሆንኩ በህይወቴ እንዳገለግለውና እርሱ በሚጠብቅብኝ መጠን እንድመላለስ ከመጀመሪያው ጀምሮ አቅዷል፤ በየእለቱ የእኔ ጥልቅ ፍላጎት፣ ስራ እና አላማ ይህ ነው፤ በኢየሱስ ስም፡፡ አሜን፡፡

## ለተጨማሪ ጥናት:

1 ኛ ጴጥሮስ 1:18-19; ኤፌሶን 2:10 AMPC; 1 ኛ ቆሮንጦስ 7:23

### የአንድ ዓመት የመጽሐፍ ቅዱስ  ጥናት

ገላትያ 3:1-14 & መኃልየ መኃልይ ዘሰለሞን 3-5

### የሁለት ዓመት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት

1 ኛ ጢሞቴዎስ 3:8-16 & ትንቢተ  ኤርምያስ 35

**Leave comments on today's devotional at**
***www.rhapsodyofrealities.org***





# ለመጸለይ መንፈሳችሁ ሲነሳሳ ችላ አትበሉ

እንግዲህ ለእግዚአብሔር ተገዙ፤ ዲያብሎስን ግን ተቃወሙ ከእናንተም ይሸሻል ። (ያዕቆብ 4፡7)

እንደ ክርስቲያን እግዚሃብሄር የሰጣችሁን ህይወት እንዴት በትጋት መኖር እንደምትችሉ ማወቅ አስፈላጊ ነው፣ አንዳንድ ነገሮች በእናንተ ዙሪያ ሲከሰቱ እንዴት መንፈሳዊ ምላሽን መስጠት እንዳለባችሁ ማወቅ አለባችሁ፡፡ ጸሎት አስፈላጊ የሆነውም ለዚህ ነው፡፡ ስንጸልይ የሆነ ነገር ይከሰታል፡፡ በከንቱ እንድንጸልይ በፍጹም አልነገረንም፡፡ ለመጸለይ መንፈሳችሁ ሲነሳሳ ችላ አትበሉ፡፡

መንፈስ ቅዱስ ያለው ሰው ከጊዜ ወደ ጊዜ ለመጸለይ መንፈሱ ይነሳሳል፣ ምክንያቱም መንፈስ ቅዱስ እራሱ የጸሎት መንፈስ ነው፣ እንዴት መጸለይ እንዳለብን ያስተምረናል፣ ደግሞም በእኛ በኩል ይጸልያል፡፡ ልባችን እንድንጸልይ ያነቃቃል፣ የምንጸልይበትንም ቃል በአፋችን ያስቀምጣል፡፡ በመንፈስ የተመራ ህይወት እስካላችሁ ድረስ፣ ሁሌም ለመጸለይ ተነሳሽነት ይኖራችኋል፡፡ አለበለዚያ እንዴት ዲያቢሎስን ትቋቋሙታላችሁ?

ዲያቢሎስ መንፈስ ነው፣ በጡንቻ ወይንም በሰውነት ጥንካሬ አንቋቋመውም፡፡ ምድራዊ በሆኑ ነገሮች አንቋቋመውም፣ የምንቋቋመው በእምነታችን ነው፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፡- “ዲያቢሎስን ተቃወሙት ከእናንተም ይሸሻል” (ያዕቆብ 4፡7)፡፡ አማራጭ የለውም፣ ከኢየሱስ ስም የተነሳ እኛን ይፈራናል፡፡

በእናንተ ህይወት፣ በምትወዷቸው ሰዎች ህይወት፣ በከተማችሁ ወይንም በሃገራችሁ ላይ የሰይጣንን እንቅስቃሴዎች ሽባ ለማድረግ የተሰጣችሁን ከፍ ያለ ኃይል ስትረዱ፣ መጸለይ ትወዳላችሁ! በስንፍና ተቀምጣችሁ ዲያቢሎስ አካባቢያችሁን ሲያወድመው አትመልከቱ፡፡ ጸልዩ። እርሱን ለመቃወም የኢየሱስ ክርስቶስን ስም ተጠቀሙ፡፡

በጸሎት ከእግዚሃብሄር ጋር ህብረት ስታደርጉ፣ ስለምትጸልዩባቸው

ነገሮች እና እንዴት እንደምትጸልዩ መንፈስ ቅዱስ ይመራችኋል፡፡ በመንፈሳዊው አለም ነገሮችን እንዴት እንደምትቆጣጠሩ ያስተምራችኋል። ሃሌሉያ!

## ጸሎት

የተባረክህ አምላክ ሆይ፣ የመጸለይን መብት እና በልሳን የመጸለይ በረከትን ስለሰጠኸኝ አመሰግንሃለሁ፡፡ በጸሎት፣ በሰማይ እንደሆነው ሁሉ ፈቃድህ በምድር መጽናቱን ለማረጋገጥ እና ባህሪህ እና ማንነትህ በእኔ በኩል እንዲገለጥ፣ ለመንፈስ ቅዱስን ምሪትና አነሳሽነት ምላሽ እሰጣለሁ፤ በኢየሱስ ስም፡፡ አሜን፡፡

## ለተጨማሪ ጥናት:

1 ኛ ተሰሎንቄ 5:17; 1 ኛ ቆሮንጦስ 14:2; ሮሜ 8:26-27

### የአንድ ዓመት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት

ገላትያ 3:15-25 & መኃልየ መኃልይ ዘሰለሞን 6-8

### የሁለት ዓመት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት

1 ኛ ጢሞቴዎስ 4:1-8 & ትንቢተ ኤርምያስ 36

**Leave comments on today's devotional at**
***www.rhapsodyofrealities.org***



ቅዳሜ 19

# በክርስቶስ ስላላችሁ ሕይወት እወቁ

> በፍርድ ቀን ድፍረት ይሆንልን ዘንድ ፍቅር በዚህ ከእኛ ጋር ተፈጽሞአል፤ እርሱ እንዳለ እኛ ደግሞ እንዲሁ በዚህ ዓለም ነን ። (1ኛ ዮሐንስ 4፡17)

ከላይ ያለውን ጥቅስ ስታነቡ“...እርሱ እንዳለ እኛ ደግሞ እንዲሁ በዚህ ዓለም ነንና”’የሚለው እኛ ኢየሱስ ከመሞቱ በፊት የነበረውን ሳይሆን በዘላለም ሕይወት የተነሳውን ኢየሱስን እንመስላለን ነው! አሁን ከእሱ ጋር ተመሳሳይ ሕይወት አለን። መጽሐፍ ቅዱስ በ1ኛ ዮሐንስ 5፡12 ላይ እንዲህ ይላል “ልጁ ያለው ሕይወት አለው.... ” ኢየሱስ ካላችሁ የዘላለም ሕይወት አላችሁ፤ የእግዚአብሔር ሕይወት አላችሁ! ከወላጆቻችሁ የተወለዳችሁበት የስነ-ተፈጥሯዊ ሕይወት አይደለም።

ኢየሱስ በዮሐንስ 3፡3 “ሰው ዳግመኛ ካልተወለደ በቀር የእግዚአብሔርን መንግስት ሊያይ አይችልም” ያለውም ለዚያ ነው ፡፡ ተፈጥሯዊ ሕይወታችሁ የእግዚአብሔርን መንግስት ሊያይ አይችልም ሲል ወደ ገነት ስለ መሄድ እየተናገረ አልነበረም፡፡ ይልቁንም የእግዚአብሔርን መንግስት እውነታ፣ በዚህ አለም ላይ የእግዚአብሔርን ግዛት፣በዚህ አለም ላይ የምንለማመደውን የእግዚአብሔርን ሕይወትና ማንነት እየተናገረ ነበር፡፡

ዳግም ስትወለዱ የእግዚአብሔርን መንግስት አሁን በዚህ ሕይወት እየተላማመዳችሁ ነው፤ ይህም የየእለት ልምምዳችሁ፣ የየዕለት ምልልሳችሁ ይሆናል። ክርስትና ይህ ነው። ክርስቶስ በግልጽ በእናንተ ውስጥ ህያው ነው፣ ከእርሱ ጋር ላትለያዩ አንድ ሆናችኋል። በ1ኛ ቆሮንቶስ 6፡17 እንዲህ ይላል “ከጌታ ጋር የሚተባበር ግን አንድ መንፈስ ነው።”

ከጌታ ጋር አንድ መንፈስ ከሆናችሁ ቫይረስን፣ ባክቴሪያን፣ ጀርምን ወይም አለምን የሚያሸብረውን የትኛውንም ነገር እንዴት ትሰጋላችሁ? ለዚህ ነው ዮሐንስ በውስጣችሁ ያላችሁን ነገር እንድታውቁ የሚፈልገው። እንዲህ አለ “የዘላለም ሕይወት እንዳላችሁ ታውቁ ዘንድ በእግዚአብሔር

ልጅ ስም ለምታምኑ ይህን ጽፌላችኋለሁ”(1ኛ ዮሐንስ 5፡13)።

በክርስቶስ ማን መሆናችሁን ስትረዱ፣ መታመም ለእናንተ እንደማይቻል ትገነዘባላችሁ። በክርስቶስ ያላችሁን ሕይወት አንዴ እውቅና ከሰጣችሁት እና በዚያ ንቃተ-ህሊና ከኖራችሁ በዚህ አለም የምትፈሩበት አንዳች ነገር አይኖርም፤ ምክንያቱም እናንተ የማትጠፉ ናችሁ። ምን አይነት ሕይወት ነው የሰጠን! ሃሌ ሉያ!

## የእምነት አዋጅ

ድንቅ የሆነ፣ የማይበሰብስ፣ የማይጠፋ፣ ተኣምራዊ የሆነ የእግዚአብሔር ሕይወት በእኔ ውስጥ አለ! የመለኮት ዝርያ ተካፋይ ነኝ፡፡ የመለኮት ባህሪ በእኔ እየሰራ ነው፣ ይህ መለኮታዊ ሕይወት በእኔ ውስጥ ስር እየሰደደ በሽታን፣ ህመምን፣ ድካምን፣ ሞትን፣ ድህነትን እና የትኛውንም ከክርስቶስ ወንጌል ጋር ተጻራሪ የሆኑ ነገሮችን ሁሉ እየገፋ ከሰውነቴ ሁሉ ያስወግዳል። እኔ የማልበገር፣ የማልሸነፍ እና የማልሰበር ነኝ። ሃሌ ሉያ!

## ለተጨማሪ ጥናት:

1 የዮሐንስ ወንጌል 5:11-13; 1 ኛ ቆሮንጦስ 15:47-49 AMPC

| የአንድ ዓመት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት |
|---|
| ገላትያ 3:26-4:1-20 & ትንቢተ ኢሳያስ 1-2 |

| የሁለት ዓመት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት |
|---|
| 1 ኛ ጢሞቴዎስ 4:9-16 & ትንቢተ ኤርምያስ 37 |

**Leave comments on today’s devotional at**
***www.rhapsodyofrealities.org***



## እሁድ 20

# በደሙ ተገዝታችኋል

> በዋጋ ተገዝታችኋልና ለራሳችሁ አይደላችሁም፤ስለዚህ የእግዚአብሔር ናቸውና በሥጋችሁና በመንፈሳችሁ እግዚአብሔርን አክብሩ። (1ኛ ቆሮንቶስ 6፡20)

በ1ኛ ቆሮንቶስ 11፡25 ላይ መጽሐፍ ቅዱስ እንዳሰፈረው ኢየሱስ “ከእራት በኋላ ጽዋውን ደግሞ አንሥቶ፦ይህ ጽዋ በደሜ የሚሆን አዲስ ኪዳን ነው፤በጠጣችሁት ጊዜ ሁሉ ይህን ለመታሰቢያዬ አድርጉት አለ።” የእሱ ደም የእሱን ሕይወት ይወክላል፤ እኛ እንድንኖርበት እርሱ ሕይወቱን ሰጥቶናል። ይሄ እናንተ ለእግዚአብሔር ምን ያክል አስፈላጊ መሆናችሁን እንድታውቁ ያደርጋል። መጽሐፍ ቅዱስ በወርቅና በብር ወይም በከበረ ድንጋይ እንዳልተገዛን ነገር ግን ውድ በሆነው በክርስቶስ ደም፣ በህያው በእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ ይነግረናል። (1ኛ ጴጥሮስ 1፡18-19)

“የጌታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን ቸር ስጦታ አውቃችኋልና፤ሀብታም ሲሆን፥እናንተ በእርሱ ድህነት ባለጠጎች ትሆኑ ዘንድ ስለ እናንተ ድሀ ሆነ።”(2ኛ ቆሮንቶስ 8፡9) በአእምሯችሁ ሊኖር የሚገባው በሕይወታችሁ በጣም አስፈላጊ የሆነ ነገር እውነተኛ ዋጋችሁ ሕይወቱን የሚወክለው የእርሱ ደም መሆኑ ነው። ከዚያ ደም የተነሳ ተጠብቃችኋል። እናንተ የእግዚአብሔር ንብረት ናችሁ፤ ስለዚህ ከከሳሾቻችሁ ትእዛዝ ወይም ከኃጢአት ተጽእኖ በታች የተተዋችሁ አይደላችሁም።

ደሙ ጽድቃችሁን ይናገራል። በእርሱ ደም ነጽታችኋል፤ ተጠብቃችሁማል። መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፤“የዘላለምን ቤዛነት አግኝቶ አንድ ጊዜ ፈጽሞ ወደ ቅድስት በገዛ ደሙ ገባ እንጂ በፍየሎችና በጥጆች ደም አይደለም” (ዕብራውያን 9፡12)፡፡ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ውድ ደም እግዚአብሔር ይመስገን።ሃሌ ሉያ!

## የእምነት አዋጅ

የኢየሱስ ደም ስርየትን፣ ጽድቅን፣ መቤዠትን፣ መግባትን፣ ህብረት ማድረግን፣ መንጻትን እና የአዲስ ኪዳን በረከቶችን ሰጥቶኛል። ከቃሉ ተወልጃለሁ፤ አዲስ ፍጥረት ነኝ፤ ከሰይጣንና ከአለም እንዲሁም ከሚጠፋው ስርዓቷና ከይዘቶቿ በላይ ነኝ። ሃሌ ሉያ!

## ለተጨማሪ ጥናት:

1 ኛ ጴጥሮስ 1:18-19; ዕብራውያን 10:14-20

የአንድ ዓመት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት

ገላትያ 4:21-5:1-15 & ትንቢተ ኢሳያስ 3-5

የሁለት ዓመት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት

1 ኛ ጢሞቴዎስ 5:1-10 & ትንቢተ ኤርምያስ 38

**Leave comments on today's devotional at**
***www.rhapsodyofrealities.org***





# ስማችሁ በሕይወት መዝገብ ውስጥ

> ማንምም በዚህ በትንቢት መጽሐፍ ከተጻፉት ቃሎች አንዳች ቢያጎድል፥እግዚአብሔር ከሕይወት መጽሐፍ እድሉን ያጎድልበታል ። (ራእይ 22፡19)

ብዙዎች፣ አንድ ሰው በሕይወት መጽሐፍ ስሙ የሚጻፈው ሕይወቱን ለክርስቶስ ሲሰጥ ነው ብለው ያስባሉ። ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስ የሚያስተምረን እንደዛ አይደለም። ጉዳዩ ስማችሁ በሕይወት መዝገብ ውስጥ ስለመጻፉ አይደለም፤ ችግሩ ከሕይወት መጽሐፍ ስለመሰረዝ ነው።

በዘጸአት 32፡32 ሙሴ እግዚአብሔርን እንዲህ አለ፡- "...ያለዚያ ግን ከጻፍኸው መጽሐፍህ እባክህ ደምስሰኝ" ሙሴ ስለ ሕይወት መጽሐፍ ያውቅ ነበር፤ይህ መጽሐፍ ዳግም ስትወለዱ ስማችሁ የሚጻፍበት መጽሐፍ አይደለም፤ ምክንያቱም ሙሴ "ዳግም አልተወለደም" ነበር፡፡ ስለዚህ የሕይወት መጽሐፍ ምንድነው? እግዚአብሔር ወደዚህ አለም የተወለደን ሰው ሁሉ የሚመዘግብበት መጽሐፍ ነው።

የመከፈቻ ጥቅሳችንን እንደገና እናንብብ፤ ለሁሉም ሰው ማስጠንቀቂያ ነበር። የእግዚአብሔር የመጀመሪያ እቅድ የነበረው እያንዳንዳችን ከእርሱ ጋር እንድንሆን ነበር። መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል "...ነገር ግን ሁሉ ወደ ንስሐ እንዲደርሱ እንጂ ማንም እንዳይጠፋ ወዶ ስለእናንተ ይታገሣል።" (2ኛ ጴጥሮስ 3፡9) የዘላለም እሳት ለሰው ፈጽሞ የተዘጋጀ አልነበረም (ማቴዎስ 25፡41) ለዲያቢሎስና ለመላእክቶቹ እንጅ። ነገር ግን እግዚአብሔር ለሰው የመምረጥን ስልጣን ሰጥቷል።

ከጊዜ በኋላ ማናቸውም በሕይወት መጽሐፍ ውስጥ ስማቸው ያልተገኘላቸው መውቀስ ያለባቸው ራሳቸውን ነው። አስቀድመን በዘጸአት 32፡33 እንዳነበብነው ለሙሴ የእግዚአብሔር መልስ የነበረው "የበደለኝን እርሱን ከመጽሐፌ እደመስሰዋለሁ" ነው፡፡ በቀላሉ ይህ ማለት ሕይወታችሁን ለእግዚአብሔር መኖር አለባችሁ ማለት ነው።

ሁልጊዜ በፍቅር፣ በጽድቅ ተመላለሱ፤ እናም ስማችሁ በሕይወት መጽሐፍ ውስጥ ይኖራል። ኢየሱስ ክርስቶስን የሚያከብር ሕይወት ኑሩ። 2ኛ ቆሮንቶስ 5፡15 እንዲህ ይላል፤ "በሕይወትም ያሉት ስለ እነርሱ ለሞተውና ለተነሣው እንጂ ወደፊት ለራሳቸው እንዳይኖሩ ስለ ሁሉ ሞተ።"

## ጸሎት

ታማኝ እና ጻድቅ አባት ሆይ፣ ማዳን ስለሚችለው ኃይልህ ምስክር እንድሆን እድልን ስለሰጠኸኝ አመሰግንሃለሁ፡፡ ዛሬ በአለም ዙሪያ ያሉ ነፍሳት ሁሉ ቃልህን እንዲቀበሉና እንዲለወጡ እጸልያለሁ። በመንግስትህ ያለኝ ስራና ከአንተ ጋር ያለኝ ምልልስ ለክብርህ በመንፈስህ የነጻ እንደሆነ አውጃለሁ፤ በኢየሱስ ስም። አሜን።

## ለተጨማሪ ጥናት:

ትንቢተ ኢሳያስ 50:7 TLB; የማርቆስ ወንጌል 10:29-30; የዮሐንስ ራዕይ 3:5

**የአንድ ዓመት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት**

ገላትያ 5:16-26 & ትንቢተ ኢሳያስ 6-8

**የሁለት ዓመት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት**

1 ኛ ጢሞቴዎስ 5:11-18 & ትንቢተ ኤርምያስ 39

**Leave comments on today's devotional at**
***www.rhapsodyofrealities.org***

# ማስ ወሻ

# ማስ ወሻ



ማክሰኞ 22

# ሁልጊዜ በመንፈስ ንቁ እና የተነሳሳችሁ ሁኑ

> በመጠን ኑሩ ንቁም፥ባላጋራችሁ ዲያብሎስ የሚውጠውን ፈልጎ እንደሚያገሣ አንበሳ ይዞራልና፤ (1ኛ ጴጥሮስ 5፡8)

በሆነ ቀን ኢየሱስ ከምኩራቦች በአንዱ ሆኖ ያስተምር ነበር፤ ቀና ማለት ያልቻለች አንድ ያጎነበሰች ሴትን ተመለከተ። በዚህ ሁኔታ ለአስራ ስምንት አመታት ቆይታለች። ኢየሱስም "አንቺ ሴት፥ከድካምሽ ተፈትተሻል አላት፥እጁንም ጫነባት፤ያን ጊዜም ቀጥ አለች፥ እግዚአብሔርንም አመሰገነች" (ሉቃስ 13፡12-13)፡፡

ኢየሱስ ያቺን ሴት በሰንበት ቀን በመፈወሱ የሀይማኖት መሪዎች ቢበሳጩም የጌታ መልስ ግን አንድ የሚገርም ነገር ገለጠ። እንዲህ አለ"... ይህችም የአብርሃም ልጅ ሆና ከአሥራ ስምንት ዓመት ጀምሮ ሰይጣን ያሰራት በሰንበት ቀን ከዚህ እስራት ልትፈታ አይገባምን?" (ሉቃስ 13፡16)

ጌታ ያችን ሴት በዚያ ሁኔታ "በድካም መንፈስ" አስሮ ያስቀመጣት ሰይጣን እንደሆነ በግልጽ ተናግሯል። ኢየሱስ መንፈሱን ሲመታው ያቺ ሴት ቀና አለች፤ በእግዚአብሔር ሃይል ሙሉ ጤነኛ ሆነች።

ኢየሱስ የመንፈሱን አለም ተረድቶታል። ሕይወት መንፈሳዊ መሆኑን ያውቅ ነበር፤ እርኩሳን መናፍስት እንዳሉ እና ለብዙ ሰዎች ስቃይ ተጠያቂ እንደሆኑም ያውቃል። በእግዚአብሔር ቃልና በመንፈስ ቅዱስ በተሰጠን ጥልቅ እይታ ሰይጣንንና ስራውን እንዴት መለየት እንዳለብን እናውቃለን።

የመጽሐፍ ቅዱስን አስተምህሮ የማታውቁ ከሆነ ለሰይጣን ሀሳብ ሰለባ ትሆናላችሁ። ቃሉን ሁልጊዜ አጥኑ አሰላስሉ፤ ሁልጊዜ በልሳን ተናገሩ፤ በመንፈስ ተሞሉ እናም መንፈሳዊ ንቃታችሁና እና ተነሳሽነታችሁ በከፍታው ላይ ይሆናል። ሕይወት መንፈሳዊ ደርዞች አሉት። ከእግዚአብሔር የሚፈልቀውንና ከዲያብሎስ የሚመጣውን ለይታችሁ ማወቅ አለባችሁ። መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፡- "የእርሱን (የሰይጣንን) አሳብ አንስተውም"

(2ኛ ቆሮንቶስ 2፥11)

## የእምነት አዋጅ

በክርስቶስ በተሰጠኝ ስልጣን ሰይጣንንና ሰራዊቱን ከእግሬ በታች አደርጋቸዋለሁ። በመለኮታዊ ጤንነት፣ በሰላም፣ በደህንነት፣ በሙላት እና በደስታ በእግዚአብሔር ክብር ውስጥ እኖራለሁ። ዛሬ በወንጌሉ በረከት ሙላት ውስጥ እመላለሳለሁ። ሃሌ ሉያ!

## ለተጨማሪ ጥናት:

ያዕቆብ 4:7; 1 ኛ ጴጥሮስ 5:8-9; 1 የዮሐንስ ወንጌል 4:4

የአንድ ዓመት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት

ገላትያ 6:1-18 & ትንቢተ ኢሳያስ 9-10

የሁለት ዓመት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት

1 ኛ ጢሞቴዎስ 5:19-25 & ትንቢተ ኤርምያስ 40

**Leave comments on today's devotional at**
***www.rhapsodyofrealities.org***






# በክርስቶስ ውስጥ መኖር

> እንግዲህ ጌታን ክርስቶስ ኢየሱስን እንደተቀበላችሁት በእርሱ ኑሩ ። (ቆላስይስ 2፡6)

ጳውሎስ ከላይ ባለው አስገራሚ ጥቅስ ያስቀመጠውን ከማየታችን በፊት በ20ኛው ቁጥር ላይ ምን እንዳለ እናንብብ፤ "ከዓለማዊ ከመጀመሪያ ትምህርት ርቃችሁ ከክርስቶስ ጋር ከሞታችሁ፥በዓለም እንደምትኖሩ ስለ ምን ትገዛላችሁ" (ቆላስይስ 2፡20)። አስገራሚ ንግግሩን አስተውሉ፤ክርስቲያን ተፈጥሯዊ በሆነ በዚህ አለም የሕይወት ደርዝ አይኖርም እያለን ነው። ክርስቲያን የሚኖረው ታዲያ የት ነው? ክርስቲያን የሚኖረው በክርስቶስ ውስጥ ነው።

ዳግም ለተወለደ ሰው፣ ክርስቶስ አዲስ የመኖሪያ ቦታና አካባቢ ነው። 2ኛ ቆሮንቶስ 5፡17 እንዲህ ይላል፤ "ስለዚህ ማንም በክርስቶስ ቢሆን አዲስ ፍጥረት ነው…"፤ ክርስቶስ ስፍራ ነው። እናንተ በተለየ መኖሪያ ስለምትኖሩ በዚህ አለም መመሪያዎች ልትጠቁ፣ ልትመሩ ወይም ተጽእኖ ሊደረግባችሁ አይገባም።

በዚያ መኖሪያ ውስጥ ሁሉም ነገር ፍጹም የሆነ ነው፤ ውድቀት፣ ድካም፣ ሽንፈት፣ ሕመም፣ በሽታ፣ ድህነት ወይም የትኛውም ከጨለማ የሆነ ነገር የለም። ያለው የእግዚአብሔር ክብርና ጽድቅ ብቻ ነው ፡፡

በመክፈቻ ጥቅሳችን ላይ ያነበብነውን አሁን በደንብ ተረድታችኋል፤ "እንግዲህ ጌታን ክርስቶስ ኢየሱስን እንደተቀበላችሁት በእርሱ ኑሩ"፡፡ በክርስቶስ ውስጥ መኖር በሁኔታዎች ላይ በፍጹም የበላይነት፤ በእርሱ የመለኮታዊ ሃይል በመከበብ፣ በእንክብካቤ እና በመጠበቅ በምድር ላይ የሰማይን መንግስት መኖር ማለት ነው።

## ጸሎት

ክርስቶስ የመኖርያ ቤቴ ነው፤ ክርስቶስ ሕይወቴ ነው፤ ክርስቶስ ሁሉ ነገሬ ነው! በእርሱ እኖራለሁ፣ እንቀሳቀሳለሁ፣ በእርሱም ህያው ነኝ። የማየው፣ ያለኝ እና የምለማመደው ክብሩን ነው። ለሁኔታዎች የተገዛሁ አይደለሁም፤ ይልቁን በክርስቶስ ክብርና ጽድቅ እገዛለሁ፤ እገለጣለሁ፤ በኢየሱስ ስም። አሜን።

## ለተጨማሪ ጥናት:

ፊልጵሱዮስ 3:20-21 AMPC; ሮሜ 8:1; 2 ኛ ቆሮንጦስ 5:17

**የአንድ ዓመት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት**

ኤፌሶን 1:1-14 & ትንቢተ ኢሳያስ 11-12

**የሁለት ዓመት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት**

1 ኛ ጢሞቴዎስ 6:1-16 & ትንቢተ ኤርምያስ 41

**Leave comments on today's devotional at**
***www.rhapsodyofrealities.org***





## እናንተ የምታበሩበት ጊዜ

> እናንተ የዓለም ብርሃን ናችሁ።በተራራ ላይ ያለች ከተማ ልትሰወር አይቻላትም ። (ማቴዎስ 5፡14)

ይሄ አለም በመንፈሳዊ ጨለማ ውስጥ ያለ አለም ነው። በኢየሱስ ጊዜም ተመሳሳይ ነበር። በተያዘ ጊዜ ያለውን አስታውሱ፡- "... ይህ ግን ጊዜያችሁና የጨለማው ሥልጣን ነው አላቸው።" (ሉቃስ 22፡53 ሕያው ትርጉም)፡፡ ኢየሱስ ወደ ሰማይ ከአረገ በኋላ አለም አሁንም በዛው በጨለማ ውስጥ ነው። ነገር ግን ለዚያ ጨለማ መፍትሄ እናንተ ናችሁ። የኢየሱስን ቃል በመከፈቻ ጥቅሳችን እንዳነበብነው እናንተ የአለም ብርሃን ናችሁ።

በመንፈስ ቅዱስ ሃይል በዚህ በመጨረሻው ዘመን ከየትኛውም ጊዜ በበለጠ ማብራት አለባችሁ። አለማችን ለዲያብሎስ አይደለችም፤ ለጌታ ለእግዚአብሔር ናት። እዚህ ያስቀመጠን ከመንፈሳዊው አለም በእርሱ ብርሃንና ጽድቅ ይሄንን አለም እንድንመራ ነው። በእምነት ስትመላለሱ፣ ቃሉን ስታሰሩ እና በክርስቶስ ያላችሁን መለኮታዊ መብትና ውርስ ስትይዙ፣ ብርሃናችሁን እያበራችሁ ነው ማለት ነው።

ይህንን አለም እያጠፋ ያለው ጨለማ፣ ሕመም፣ በሽታ፣ ድህነት፣ የደህንነት ስጋት ምንም ግድ አይበላችሁ፤ በዚህ አለም ላይ በቃሉ አማካኝነት በክርስቶስ እንድትገዙና እንድትነግሱ ስልጣን ተሰጥቷችኋል። ሌሎች እናንተን በማየት ትክክለኛ ክርስቲያን ማን እንደሆነ ይረዳሉ፡፡ በእናንተ ውስጥ የክርስቶስን ክብርና ልህቀት ያያሉ።

ኢሳይያስ 60፡1-2 እንዲህ ይላል፤ "ብርሃንሽ መጥቶአልና፥የእግዚአብሔርም ክብር ወጥቶልሻልና ተነሺ፣አብሪ። እነሆ፥ጨለማ ምድርን ድቅድቅ ጨለማም አሕዛብን ይሸፍናል፤ነገር ግን በአንቺ ላይ እግዚአብሔር ይወጣል ክብሩም በአንቺ ላይ ይታያል"፡፡ በእግዚአብሄር ቃል እንደተረጋገጠው፣ በጽድቅ፣ በብልጽግና፣ በጤና ፣ በጤናማ አእምሮና አካል በመመላለስ በጨለማው አለም ላይ ብርሃናችሁ

የሚበራበት ጊዜው አሁን ነው፡፡

## ጸሎት

እኔ የአለም ብርሃን ነኝ፤ ለአለሜ ብርሃንን የምሰጥ በተራራ ጫፍ ላይ የተቀመጠች ከተማ ነኝ። በእኔ ውስጥ እና በእኔ በኩል የክርስቶስ ክብሩና ጽድቁ ይገለጣሉ፡፡ በብልጽግና፣ በበረከት፣ በትክክለኛ አእምሮና አካል እመላለሳለሁ፤በኢየሱስ ስም። አሜን።

## ለተጨማሪ ጥናት:

ትንቢተ ኢሳያስ 60:1-3; የዮሐንስ ወንጌል 9:5; ፊልጵሱዮስ 2:15; 1 ኛ ተሰሎንቄ 5:5

### የአንድ ዓመት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት

ኤፌሶን 1:15-2:1-10 & ትንቢተ ኢሳያስ 13-14

### የሁለት ዓመት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት

1 ኛ ጢሞቴዎስ 6:17-21 & ትንቢተ ኤርምያስ 42

**Leave comments on today's devotional at**
***www.rhapsodyofrealities.org***



አርብ 25

# የእግዚአብሄርን ጊዜ መረዳት

> እርሱም እንዲህ አለኝ። ዳንኤል ሆይ፥ አትፍራ፤ ልብህ ያስተውል ዘንድ፥ ሰውነትህም በአምላክህ ፊት ይዋረድ ዘንድ ካደረግህበት ከመጀመሪያው ቀን ጀምሮ ቃልህ ተሰምቶአል፤ እኔም ስለ ቃልህ መጥቻለሁ። (ዳንኤል 10፡12)

እኛ ያለነው በእግዚህብሔር መንግስት ውስጥ እጅግ ልዩ በሆነ ጊዜ ውስጥ ነው፡፡ በቃሉ እውቀት አማካኝነት በመንፈስ በመመራት በእርሱ እቅድና ጊዜ መሰረት እንራመዳለን፡፡

ለምሳሌ በዳንኤል ምዕራፍ 9፤ ዳንኤል የነብዩ ኤርሚያስን መፅሀፍ ሲያጠና፣ ከእስራኤል ህዝብ ጋር በስደት ባለበት ወቅት፣ የእግዚህብሄርን ጊዜ እንደተረዳ መፅሀፍ ቅዱስ ይነግረናል፡፡ በምርኮኝነትም ለሰባ አመታት እንደሚቆዩ እና የምርኮ ጊዜያቸውም እንዳበቃ ተረድቶ ነበር፡፡

ነገር ግን ምንም እንዳልተቀየረ ሲገነዘብ፣ ዳንኤል በፆም እና በፀሎት የእግዚአብሄርን እቅድ እውን ለማድረግ ወሰነ፡፡ በመጨረሻም በፆም እና በፀሎት ወደ እግዚአብሄር መጣ፡፡

በእስራኤል ኢየሱስ በነበረው የመጨረሻዎቹ የአገልግሎቱ ቀናት፤ ለእየሩሳሌም አነባ፤ ምክንያቱም በመከፈቻ ጥቅሳችን እንዳነበብነው የመጎብኘታቸውን “ጊዜ” አላወቁም ነበርና፡፡ ሲጠብቁት የነበሩት ጌታ፤ ወደእነርሱ መጥቷል፣ ነገር ግን አላወቁትም፡፡ እንዴት አሳዛኝ ነው፡፡ ዛሬ ብዙዎች እንደዛ ናቸው፡፡

ህይወታችሁ እግዚአብሄር ለእናንተ ካለው አላማ እና ጊዜ ጋር እንዲጣጣም ለማድረግ ቅድሚያ ስጡ፡፡ ጥቅሶችን በጉጉት አጥኑ፤ እናም ለፀሎት ጊዜ ስጡ፡፡ እኛ የኢየሱስን ስምና የመንፈስ ቅዱስ ኃይልን በመጠቀም በምድር ላይ የእግዚአብሄርን አላማ እናሳካ ዘንድ በእርሱ የተላክን ነን፡፡

የእግዚአብሄርን ፍቃድ እና ጊዜ ግን የማታውቁ ከሆናችሁ፤ የእናንተም የጌታም ፍላጎት ያልሆኑ ነገሮች በምድር ላይ ይከሰታሉ፡፡ በመንፈስ ለሀገራት፣ ለቤተክርስትያን እና በአለም ዙሪያ ላሉ ለወንጌል አገልጋዮች

መጸለይ ያለባችሁም ለዚህ ነው፡፡ መንግስቱ በእናንተ ላይ የተመረኮዘ ያህል ቆጥራችሁ ፀልዩ፤ ደግሞም እንደዚያው ነው፡፡

## ጸሎት

ውድ አባት ሆይ፤ በቤተክርስትያን መነጠቅ ስለሚጠናቀቀው፣ የአንተ ተአምራዊ ወቅቶች እና ከዚህ በፊት ሆኖ በማያውቅ ሁኔታ ስለሚገለጡ የአንተ ስራዎችና በረከቶች አመሰግናለሁ፡፡ በዓለም ዙርያ በከባድ ስደትና በኢ-ፍትሃዊ ሁኔታ ውስጥ ላሉ ቅዱሳን ሁሉ፣ በእግዚአብሄር ፈቃድ ጠንክረውና ጸንተው እንዲቆሙ እፀልያለሁ፤ በእየሱስ ስም፡፡ አሜን፡፡

## ለተጨማሪ ጥናት:

ትንቢተ ዳንኤል 9:2-4; 1 ኛ ጴጥሮስ 5:8-9; መጽሀፈ ዜና መዋዕል ቀዳማዊ 12:32

**የአንድ ዓመት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት**

ኤፌሶን 2:11-22 & ትንቢተ ኢሳያስ 15-18

**የሁለት ዓመት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት**

2 ኛ ጢሞቴዎስ 1:1-18 & ትንቢተ ኤርምያስ 43

**Leave comments on today's devotional at**
***www.rhapsodyofrealities.org***





# ስለመለኮታዊ ባህርያችሁ ንቃተ ህሊና



ልጆች ሆይ፥ እናንተ ከእግዚአብሔር ናችሁ አሸንፋችኋቸውማል፥ በዓለም ካለው ይልቅ በእናንተ ያለው ታላቅ ነውና። (1ኛ ዮሐንስ 4፡4)

ከላይ የተጠቀሰው ጥቅስ "እናንተ ከእግዚአብሄር ናችሁ..." ሲል፣ ብዙዎች የመንፈስን ቋንቋ አይረዱትም፤ ይህም ማለት እናንተ የመጣችሁት ከእግዚአብሄር ነው ማለት ነው፤ የተወለዳችሁት ከእርሱ ነው ማለት ነው፡፡ ክርስትያንን እንዲሁ ተራ ሰው ሳይሆን፣ መለኮታዊ ማንነት ያለው የሚያደርገውም ያ ነው፡፡ ሀሌሉያ፡፡

አንዳንዶች የሳቱት ይህንን ነው፤ በክርስቶስ ማን እንደሆኑ ንቃተ ህሊና የላቸውም፡፡ ሀዋሪያው ዮሀንስ ይህንን በተመለከተ በ1ኛ ዮሀንስ 5፡13 ላይ እንዲህ አለ፡- "የዘላለም ሕይወት እንዳላችሁ ታውቁ ዘንድ በእግዚአብሔር ልጅ ስም ለምታምኑ ይህን ጽፌላችኋለሁ።" እግዚአብሄር የእርሱ ህይወት በእናንተ ውስጥ እንዳለ የነቃ የሚሰራ እውቀት እንዲኖራችሁ ይፈልጋል፡፡ እናንተ የመለኮታዊ ህይወት ተሸካሚዎች፣ እግዚአብሄርን ማስተላለፊያዎች ናችሁ፡፡

ጌታ እየሱን በተመለከተ መጽሀፍ ቅዱስ በቆላስይስ 2፡9-10 "በእርሱ የመለኮት ሙላት ሁሉ በሰውነት ተገልጦ ይኖራልና። ለአለቅነትና ለሥልጣንም ሁሉ ራስ በሆነ በእርሱ ሆናችሁ ተሞልታችኋል" ይላል፡፡ አገላለጹን አስተውሉ "በእርሱ ሆናችሁ ተሞልታችኋል..."፡፡ ይህ ማለት ልክ በክርስቶስ ውስጥ እንዳለው የመለኮት ሙላት በእናንተም ውስጥ አለ። ምንም ጥያቄ የለውም ጴጥሮስ "እግዚአብሄርን ከሚመስሉ ጋር ህብረት ያለው፣ "ከመለኮት ባሕርይ ተካፋዮች" (2ኛ ጴጥሮስ 1፡4) ብሎ ቢጠራን አያስገርምም፡፡

በእግዚአብሄር ተሞልታችኋል፡፡ በእርሱ "ሙሉ መሆን" ማለት ይህ ነው፤ መለኮታዊ እንድትሆኑ ሌላ በእናንተ ውስጥ ሊኖር የሚገባ ነገር የለም። ህመም፣ በሽታ፣ ወይም ድካም የህይወታችሁ አካል ሊሆን የማይችለውም

ለዚህ ነው፡፡ በውስጣችሁ ያለውን የእግዚአብሄር ህይወት ብታሰላስሉ፣ በህይወታችሁ ለአንድም ቀን አትታመሙም፡፡

እናንተ ከእግዚአብሔር ተወለዳችሁ እንጂ ከደም ወይም ከሥጋ ፈቃድ ወይም ከወንድ ፈቃድ አልተወለዳችሁም፡፤ (ዮሀ 1፡13፡፡ እግዚአብሄር መታመም ወይም መሸነፍ ወይንም ምንም ነገር "እንዳይሆንበት" ያደረገው ያው ህይወት በእናንተ ውስጥም ያለው ነው፡፡ የዚህ አስተሳሰብ እውነታ በእናንተ ውስጥ ሲኖር ለዘላለም አሸናፊና እያንዳንዱን የህይወታችሁን ቀኖች በሙሉ በበላይነት እንድትመላለሱ ያደርጋችኋል፡፡፡ ክብር ለእግዚአብሄር ይሁን!

## የእምነት አዋጅ

እግዚአብሄር ይባረክ፤ መለኮታዊ ባህርይ አለኝ፤ በዚያም ንቃተ ህሊና እመላለሳለሁ፡፡ ከበሽታ፣ ከህመም፣ ከሞት እና ከዚህ አለም ሁኔታዎች የበላይ ሆኜ በድል እራመዳለሁ፡፡ ክርስቶስ በእኔ ውስጥ ከሁሉ ይበልጣል፤ ዛሬም ሁሌም ከጌታ ጋር ያለኝን አንድነት አከብራለሁኝ፤ በእየሱስ ስም፡፡ አሜን፡፡

## ለተጨማሪ ጥናት:

2 ኛ ጴጥሮስ 1:4; የዮሐንስ ወንጌል 5:26; 1 የዮሐንስ ወንጌል 5:11-13

**የአንድ ዓመት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት**

ኤፌሶን 3:1-21 & ትንቢተ ኢሳያስ 19-22

**የሁለት ዓመት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት**

2 ኛ ጢሞቴዎስ 2:1-10 & ትንቢተ ኤርምያስ 44

**Leave comments on today's devotional at**
***www.rhapsodyofrealities.org***





# ልክ እንደ ህፃን ተማመኑ

> በፍጹም ልብህ በእግዚአብሔር ታመን፥ በራስህም ማስተዋል አትደገፍ ። (ምሳሌ 3፡5)

የተማመነ ማለት የሚደለል ማለት አይደለም፤ የእነዚህን ልዩነት ማወቅ በጣም አስፈላጊ ነው፤ ምክንያቱም አንዳንዶች የታመኑ መስለው ግን የሚደለሉ አሉ፡፡ የሚደለል ማለት በቀላሉ የሚታለል ሰው ማለት ነው፡፡ ነገር ግን ልጆች በቀላሉ አይታለሉም፣ ነገር ግን ይተማመናሉ፤ ያላችሁ ባህሪ ላይ ይተማመናሉ፡፡ አዋቂዎች ግን በቀላሉ የሚታለሉ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ አዋቂ ሰው ግን የሚነገረውን ከመተማመኑ በፊት ምክንያታዊነቱን ለማወቅ ይሞክራል፤ ስላመነው ሰው ባህሪያት እምብዛም ግድ ላይለው ይችላል፡፡

ለምሳሌ አንድን ህፃን ልጅ ከፎቅ ላይ ይዛችሁት፣ ህጻኑ የሚያምነው አንድ ሰው ምድር ላይ ሆኖ እንዲይዘው ብታቆሙ፤ ህጻኑ ወደታች ለመውረድ ዝግጁ ይሆናል፤ ምክንያቱም መሬት ላይ በቆመው ሰው ስለሚተማመን ነው፡፡ ህፃኑ ታች የቆመው ሰው እርሱን ለመቅለብ ሀይል ወይም አቅም ይኑረው አይኑረው ላያውቅ ይችላል፤ ነገር ግን እንዲወድቅ እንደማይፈቅድ ያምናል፡፡ በእግዚአብሄር ላይ ሊኖራችሁ የሚገባው እምነት፣ ይህ አይነቱ የህፃን ልጅ እምነት ነው፡፡

ጌታ ኢየሱስ በማቴዎስ 18፡3 አምፕሊፋይድ ትርጉሙ ልክ እንደልጆች መሆን እንዳለብን መክሮናል፡- “እንዲህም አለ። እውነት እላችኋለሁ፥ ካልተመለሳችሁ እንደ ሕፃናትም ካልሆናችሁ፥ ወደ መንግሥተ ሰማያት ከቶ አትገቡ፡፡” የእግዚአብሄርን ባህሪ እንድትተማመኑበት ይፈልጋል፤ ባህሪው ደግሞ በቃሉ ውስጥ ግልፅ ሆኗል፤ መቼም አይወድቅም፡፡ ለህይወታችሁ ያለውን ዓላማ ለመፈጸም በድፍረት መተማመናችሁን በእርሱ ላይ አድርጉ፡፡

አንዳንዶች እግዚአብሄር ያሰበውን ያሳካ ዘንድ ለመርዳት ይሞክራሉ። ምናልባትም ራእይ ሰጥቷችሁ ይሆናል፤ ወይም ከአላማችሁ ጋር የሚገናኝ እቅድን ወይም ሀሳብን ሰጥቷችሁ ይሆናል፤ እናም በጣም ተደስታችሁ እንዲሳካ ፈልጋችሁ ይሆናል፤ ይህ መልካም ነው! ነገር ግን የማታምኑና

እራሳችሁን ለመንፈስ ቅዱስ የማታስገዙ ከሆነ፣ "እግዚአብሄርን ለመሆን" ልትሞክሩ ትችላላችሁ፡፡ በራሳችሁ ጥበብ እርሱን ለመርዳት በመሞከር፣ የእርሱን ሚና እየተጫወታችሁ ይሆናል፡፡ ነገር ግን የዚህ የመጨረሻ ውጤት መልካም አይሆንም፡፡

ከሁሉም የሚሻለው እርሱ ብቻ እንደሚያውቅ እና የህይወታችሁን ካርታ እርሱ እንደያዘው አውቃችሁ በእርሱ መተማመን ነው፡፡ እግዚአብሄር ወዴት እንደሚመራው ሳያውቅ አምኖ ከተከተለው ከአብርሀም ትምህርት ውሰዱ፡፡ በዕብራውያን 11፡8 መፅሀፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፡- "አብርሃም የተባለው ርስት አድርጎ ሊቀበለው ወዳለው ስፍራ ለመውጣት በእምነት ታዘዘ፥ ወዴትም እንደሚሄድ ሳያውቅ ወጣ።"

## ጸሎት

ውድ አባት ሆይ፤ በቃልህ ላይ እየተደገፍኩኝ እና ትእዛዛቶችህን እየፈፀምኩኝ፤ በነገሮች ሁሉ በሙሉ ልቤ እያመንኩህ ህይወቴን እኖራለሁ፡፡ እኔ መቼም ልሆን ከምችለው በላይ፣ ስለስኬቴ የበለጠ ግድ እንደሚልህና ጥልቅ ፍላጎት እንዳለህ ሙሉ በሙሉ በማመን፤ እቅዶቼን፣ የወደፊት ራእዮቼን እና ምኞቶቼን ለአንተ አሳልፌ እሰጣለሁ፤ በኢየሱስ ስም፡፡ አሜን

## ለተጨማሪ ጥናት:

*መጽሀፈ ምሳሌ 3:5-6; መዝሙረ ዳዊት 18:30*

የአንድ ዓመት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት

ኤፌሶን 4:1-16 & ትንቢተ ኢሳያስ 23-24

የሁለት ዓመት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት

2 ኛ ጢሞቴዎስ 2:11-26 & ትንቢተ ኤርምያስ 45

**Leave comments on today's devotional at**
***www.rhapsodyofrealities.org***



ሰኞ 28

# “ምንጫችሁን” ሊደፍኑ የሚችሉ ቆሻሻዎችን እምቢ በሉ

> ከበዓሉም በታላቁ በኋለኛው ቀን ኢየሱስ ቆሞ። ማንም የተጠማ ቢኖር ወደ እኔ ይምጣና ይጠጣ። በእኔ የሚያምን መጽሐፍ እንዳለ፥ የሕይወት ውኃ ወንዝ ከሆዱ ይፈልቃል ብሎ ጮኸ። (ዮሀ 7፡38)

ኢሳያስ 12፡3 “ውኃውንም ከመድኃኒት ምንጮች በደስታ ትቀዳላችሁ።” የመዳን ምንጮች ማለት በመንፈሳችሁ ጥልቀት ውስጥ ያሉ የክርስቶስ በረከቶችን ሁሉ ይመለከታል፡፡ መፅሀፍ ቅዱስ ሲናገር ህይወት ከመንፈሳችሁ ይፈሳል ይላል፡፡ በውስጣችሁ የበረከት ፏፏቴዎችን ይዛችኋል፡፡

እናም ዲያቢሎስ ሁልጊዜ “ምንጫችሁን” ሊደፍን ይፈልጋል፡፡ በመጸሀፍ ቅዱስ ቀናት ሲሆን ከነበረው ጋር አገናዝባችሁ አስቡት፤ የወራሪ ሀይል በመጣ ቁጥር፣ ፈሪዎቹን ተስፋ ለማስቆረጥ በከተማው የሚገኙ ምንጮች በቆሻሻ ይደፍኑ ነበር፡፡ ምንጮቹ ህዝቡ ውሀ የሚያገኙበት ማለትም የህይወት ምንጭ ነበሩ፡፡

ይስሀቅም ተመሳሳይ ፈተና ከፍልስጤማውያን ገጥሞት ነበር፡፡ ይስሀቅን በተመለከተ መፅሀፍ ቅዱስ እንዲህ ሲል መዝግቦታል፡- “በአባቱ በአብርሃም ዘመን የአባቱ ሎሌዎች የማሱአቸውን ጉድጓዶች ሁሉ የፍልስጥኤም ሰዎች ደፈኑአቸው አፈርንም ሞሉባቸው። ይስሐቅም በአባቱ በአብርሃም ዘመን ቈፍረዋቸው የነበሩትን የውኃ ጉድጓዶች ደግሞ አስቈፈረ፤ አብርሃም ከሞተ በኋላ የፍልስጥኤም ሰዎች ደፍነዋቸው ነበሩና፤ አባቱም ይጠራቸው በነበረው ስም ጠራቸው።” (ዘፍጥረት 26፡15፣18)፡፡

ልክ ፍልስጤማውያን (እርሱን ተስፋ ለማስቆረጥ) የይስሀቅን የውሃ ምንጮች እንደዘጉት፤ ሰይጣንም የክርስቶስን ሀሴት በህይወታችሁ እንዳትገልጡ በማድረግ በመንፈሳችሁ ያለውን የህይወት ምንጭ ለመድፈን ይፈልጋል፡፡ ለሌሎች ሰዎችም ያንኑ ሀሴት እንዳታገለግሉ ለማድረግ

ይፈልጋል፡፡

“ምንጫችሁን” የሚዘጋበት መሳሪያዎች ደግሞ መራራነት፣ ቅናት፣ ጥላቻ፣ ቅሬታ፣ ይቅር አለማለት፣ ፍርሀት እና ሁሉን የሚኮንን ማንነት ናቸው፡፡ ሰይጣን እንደነዚህ ያሉ “ቆሻሻዎችን” ህይወታችሁ ውስጥ እንዲጥል አትፍቀዱለት፡፡ ተበሳጭታችሁ፣ ቅር ተሰኝታችሁ ወይም በከፋት ተሞልታችሁ በደስታ ልትኖሩ፣ ህይወትን ልታጣጥሙ ወይም በውጤታማነት ዓለማችሁን ልትባርኩ እንደማትችሉ ያውቃል፡፡

ይልቁኑ የእግዚአብሄር ሀሴት እና ፍቅር ከውስጣችሁ ፈስሶ ለሌሎች እንዲያንጸባርቅ ምረጡ፤ እናም ዲያቢሎስ በህይወታችሁ ምንም ስፍራ አይኖረውም፡፡

## ጸሎት

ውድ አባት ሆይ፤ በመንፈስ ቅዱስ በልቤ ውስጥ ስለፈሰሰው ፍቅርህ እና በልቤ ስላለው የክርስቶስ ሙላት አመሰግናለሁ፡፡ ግዙፍ እርምጃዎችን ወደፊት በመራመድ፣ በክብር ህይወቴን እኖራለሁ፤ በኢየሱስ ስም፡፡ አሜን፡፡

## ለተጨማሪ ጥናት:

ኤፌሶን 4:31-32; ያዕቆብ 3:15-17; ዕብራውያን 12:15

**የአንድ ዓመት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት**

ኤፌሶን 4:17-5:1-2 & ትንቢተ ኢሳያስ 25-26

**የሁለት ዓመት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት**

2 ኛ ጢሞቴዎስ 3:1-17 & ትንቢተ ኤርምያስ 46

**Leave comments on today’s devotional at**
***www.rhapsodyofrealities.org***

# ማስ ወሻ

# ማስ ወሻ





# መንፈሳችሁን ለማለማመድ የተረጋገጠ መንገድ

> ነገር ግን ለዚህ ዓለም ከሚመችና የአሮጊቶችን ሴቶች ጨዋታ ከሚመስለው ተረት ራቅ፡፡ እግዚአብሔርን ለመምሰል ግን ራስህን አስለምድ። ሰውነትን ለሥጋዊ ነገር ማስለመድ ለጥቂት ይጠቅማልና፤ እግዚአብሔርን መምሰል ግን የአሁንና የሚመጣው ሕይወት ተስፋ ስላለው፥ ለነገር ሁሉ ይጠቅማል ። (1ኛጢሞቴዎስ 4፡7-8)

እግዚአብሔርን ለመምሰል መለማመድ ማለት እውነተኛ ማንነታችሁ የሆነውን መንፈሳችሁን ማለማመድ ማለት ነው፤ እናም መንፈሳዊነታችሁን ለማለማመድ አንዱ እርግጠኛ መንገድ ደግሞ በልሳን መጸለይ ነው፡፡ ይህም መንፈሳችሁን ለእግዚአብሔር ቦግ ብሎ የተቀጣጠለ ሆኖ እንዲቆይ ያደርገዋል። በይሁዳ 1:20 እንዲህ “እናንተ ግን፥ ወዳጆች ሆይ፥ ከሁሉ ይልቅ በተቀደሰ እምነታችሁ ራሳችሁን ለማነጽ እየተጋችሁ በመንፈስ ቅዱስም እየጸለያችሁ፥” ይላል፡፡1ኛ ቆሮንቶስ 14:4 ደግሞ “በልሳን የሚናገር ራሱን ያንጻል...” ይላል፡፡

አዘውትረው በልሳን የሚጸልዩ ክርስቲያኖች ከመንፈሳዊ ነገሮች ጋር በተሻለ የተዋሃዱና በመንፈስ ቅዱስ ለመመራትም የበለጠ የተነቃቁና በቀላሉ ምላሽ ለመስጠት የተዘጋጁ ናቸው። ብዙ ጊዜ በልሳን የምትጸልዩ ከሆነ መንፈሳችሁ ለታላቅ ወንጌል ሰብከት የተነቃቃና የተዘጋጀ ነው፤ ለስንፍና ቦታ የለውም፡፡

ቀናችሁን በልሳን በመጸለይ የመጀመር ልምዳችሁን አጎልብቱ፤ እንዲሁም በቀኑ ውስጥ በተለያየ ሰአት በልሳናችሁ ጸልዩ፡፡ ደስ የሚለው ነገር ደግሞ፤ በቢሮም ሆነ በተለያየ የስራ ቦታ ሆናችሁ ድምፅ ሳታሰሙ በውስጣችሁ መናገር መቻላችሁ ነው፡፡ይህም ፈጣን የመንፈስ መቀስቀሻና ሃይል መስጫ መንገድ ነው።

አንዳንድ ሰዎች ለጸሎት ጊዜ በመስጠት መንፈሳቸውን ከማጎልበት ይልቅ በበለጠ ለሰውነታቸው መዳበር የበለጠ ይጨነቃሉ፡፡ እራሳችሁን

ደጋግማችሁ በልሳን መጸለይ በምታለማምዱበት ወቅት በሕይወታችሁ ላይ ከሚኖሩት ብዙ ሌሎች ጥቅሞች በተጨማሪ፣ መንፈሳችሁን ክፍት በማድረግ የእግዚአብሔርን ቃል እንድትቀበሉና እንድትረዱ እንዲሁም በመለኮታዊው ሕይወታችሁ በምታደርጉት ጉዞ ብርታትን ይጨምርላችኋል።

## ጸሎት

ውድ አባት ሆይ፣ ቃልህን እጅግ አድርጌ እወዳለሁ! በልሳን በመጸለይ መንፈሴን እንዴት እንደማለማምድና እንደማነቃቃ ስላሳየኸኝ አመሰግንሀለው። ዛሬ የአንተን ምሪት ለመቀበል መንፈሴ ተነቃቅቶአል፤ በሕይወቴና በአገልግሎቴ ከክብር ወደ ክብር አስገራሚ ለውጥ እያመጣሁ ነው፣ በኢየሱስ ስም፡፡ አሜን።

## ለተጨማሪ ጥናት:

1 ኛ ጢሞቴዎስ 4:7-8 AMPC; 1 ኛ ቆሮንጦስ 14:4 AMPC; ዕብራውያን 5:14

**የአንድ ዓመት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት**

ኤፌሶን 5:3-21 & ትንቢተ ኢሳያስ 27-28

**የሁለት ዓመት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት**

2 ኛ ጢሞቴዎስ 4:1-10 & ትንቢተ ኤርምያስ 47

**Leave comments on today’s devotional at**
***www.rhapsodyofrealities.org***





# በቃሉ ያለ እምነት

ኢየሱስም ለመቶ አለቃው፡-ሂድና እንዳመንህ ይሁንልህ አለው።ብላቴናውም በዚያች ሰዓት ተፈወሰ ።
(ማቴዎስ 8፥13)

በአንድ ወቅት ጌታ ከሙታን ከተነሳ በኋላ ደቀ መዛሙርቱ ፍሬ-ቢስ የሆነ አሳ የማጥመድ ተልእኮ አድርገው ሲያጠናቅቁ ጌታ ኢየሱስ ተገለጠላቸው። ደቀመዛሙርቱ ሌሊቱን ሙሉ ቢደክሙም ምንም ዓሳ መያዝ አልቻሉም ነበር። በዮሐንስ 21፥6 እንደ ተፃፈው ጌታም እንዲህ አላቸው፡- "መረቡን በታንኳይቱ በስተቀኝ ጣሉት ታገኙማላችሁ። ስለዚህ ጣሉት፤በዚህም ጊዜ ከዓሣው ብዛት የተነሣ ሊጐትቱት አቃታቸው።"

አይሆንም ብለው ጌታን ተከራክረውት ቢሆን የሚሆነውን አስቡት! እነሱ በቃሉ እምነት ነበራቸው ዓሳዎችም የመጡት ከእግዚአብሔር ቃል ነው። መፅሐፍ ቅዱስ በዕብራውያን 11:3 ላይ እንዲህ ይላል፡- "ዓለሞች በእግዚአብሔር ቃል እንደተዘጋጁ፥ ስለዚህም የሚታየው ነገር ከሚታዩት እንዳልሆነ በእምነት እናስተውላለን።" ዓሳዎቹ በጌታ ቃል እንደተዘጋጁ እናስተውላለን። ኢየሱስ ቃሉ ላይ ባለን እምነት እንዴት የተአምራት ሕይወት መለማመድ እንዳለብንና እንዲሁም በየእለቱ እንዴት በድል እንደምንኖር ቀድሞ አሳይቶናል፡፡

የሚከተለውን አስተውሉ፡- በሉቃስ 7:2-7 እንደምንመለከተው የአንድ የመቶ አለቃ አገልጋይ ታሞ ሊሞት ቀርቦ ነበር። የመቶ አለቃውም የአይሁድን ሽማግሌዎች ወደ እርሱ ላከና መጥቶ ባሪያውን እንዲያድን ለመነው። ኢየሱስም ለመሄድ ተስማማ፡፡ ነገር ግን ወዲያው የመቶ አለቃው ወዳጆቹን ወደ ኢየሱስ ላከ፤ አለውም፡- "ጌታ ሆይ በቤቴ ጣራ በታች ልትገባ አይገባኝምና አትድከም፤ ስለዚህም ወደ አንተ ልመጣ እንዲገባኝ ሰውነቴን አልቈጠርሁትም፤ነገር ግን ቃል ተናገር፥ ብላቴናዬም ይፈወሳል፡፡"

ኢየሱስም የመቶ አለቃውን ቃል በሰማ ጊዜ በእምነቱ ተደንቆ በሉቃስ 7:9—10 ላይ እንደተፃፈው "እላችኋለሁ፤ እንዲህ ያለ ትልቅ እምነት በእስራኤል እንኳ አላገኘሁም" አላቸው። የተላኩት ሰዎችም ወደ ቤት በተመለሱ ጊዜ፣ አገልጋዩን ድኖ አገኙት። የመቶ አለቃው በኢየሱስ ቃል እምነት ነበረው።

እናንተስ መሻታችሁ ምንድን ነው? በየትኛው ሕይወታችሁ ለውጥና ተአምራት ትፈልጋላችሁ? በጌታ ቃል ላይ ያላችሁን እምነት ተገልገሉበት። የእግዚአብሔር ቃል ለችግሮቻችሁ ሁሉ መፍትሔ ነው። ስራችሁን ስለለቀቃችሁ ወይንም ንግዳችሁ ስለተበላሸ እራሳችሁን ለማጥፋት ማሰብ የለባችሁም። ለተሻለና ለበለጠ ነገር በጌታ ተማመኑ። እሱ ለሙታን ሕይወትን የሚሰጥ ጌታ ነው። አጣሁት ብላችሁ ያሰባችሁትን ሁሉ ጨምሮ ጨማምሮ ይመልስላችኋል።

አሁንም ቢሆን ቃሉን በስራ ላይ አውሉት። በዮሐንስ 14፥14 ጌታ "ማናቸውንም ነገር በስሜ ብትለምኑ እኔ አደርገዋለሁ" ብሏል። ለቃሉ ታማኝ ስለሆነና ፈጽሞ የጠየቃችሁትን ከማድረግ ወደኋላ ስለማይል እናንተም ያሻችሁን ነገር ብትጠይቁ ያደርግላችኋል፡፡

## ጸሎት

ውድ አባት ሆይ፤ከሕይወት ችግሮች ሁሉ በላይ ስለሚያደርገኝና መንፈሴን በእምነት ስለሚደግፈው ውድ ቃልህ አመሰግናለሁ፡፡ ቃልህ በልቤ ውስጥ ከእምነቴ ጋር ተጣምሮአል፤ በዚህም ምክንያት እምነቴ ህያውና የተነቃቃ ነው ፤ይህም ከሁኔታዎች ሁሉ በላይ በመሆን ለእኔ ካለህ ፍጹም መለኮታዊ ፈቃድህ ጋር የተጣመረ ነው፣ በኢየሱስ ስም፡፡ አሜን።

## ለተጨማሪ ጥናት:

ሮሜ 10:17; 2 ኛ ቆሮንጦስ 4:13; ዕብራውያን 11:6

**የአንድ ዓመት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት**

ኤፌሶን 5:22-6:1-9 & ትንቢተ ኢሳያስ 29-30

**የሁለት ዓመት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት**

2 ኛ ጢሞቴዎስ 4:11-22 & ትንቢተ ኤርምያስ 48

**Leave comments on today's devotional at**
***www.rhapsodyofrealities.org***

# ማስ ወሻ

# ማስ ወሻ

# የደህንነት ጸሎት

በዚህ መጻሐፍ እንደተባረካችሁ እናምናለን፡፡ ክርስቶስ ኢየሱስን በሕይወታችሁ ጌታ እንድታደርጉ እንጋብዛችኋለን።

“ጌታ እግዚአብሔር ሆይ ኢየሱስ የሕያው እግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ፤ በሙሉ ልቤ አምናለሁ ፡፡ ለእኔ ሲል እንደሞተ እና እግዚአብሔርም ከሞት እንዳስነሳው አምናለሁ፡፡ ዛሬ ሕያው እንደሆነ አምናለሁ፡፡ ከዛሬ ጀምሮ ኢየሱስ ክርስቶስ የሕይወቴ ጌታ እንደሆነ በአፌ አውጃለሁ፡፡ በእርሱ በኩል እና በስሙ ዘላለማዊ ሕይወት አለኝ፡፡ ዳግም ተወልጃለሁ፡፡ ጌታ ሆይ ነብሴን ስላዳንካት አመሰግንሀለሁ! አሁን የእግዚአብሔር ልጅ ነኝ፡፡ ሀሌሉያ!”

**እንኳን ደስ ያልዎት፤ አሁን የእግዚአብሔር ልጅ ነዎት።**
**እንደክርስቲያን በመንፈሳዊ ሕይወትዎ እንዲያድጉ**
**ከታች በተጻፈው ስልክ ቁጥር ይደውሉ፡፡**


**UNITED KINGDOM:**
+44 (0)1708 556 604
+44 (0)08001310604

**NIGERIA:**
+234 1 8888186

**CANADA:**
+1 416-667-9191

**SOUTH AFRICA:**
+27 11 326 0971

**USA:**
+1(800) 620-8522

# ስለ ጸሃፊው

ፓስተር ክሪስ ኦያኪሎሜ፣ የተነቃቃና ባለብዙ ዘርፍ ዓለማቀፍ አገልግሎት የሚሰጠውን የቢሊቨርስ ላቭ ወርልድ ኩባንያ ፕሬዜዳንት ሲሆኑ፣ ከሰላሳ የሚበልጡ መጽሀፍት እና በአንደኝነት ደረጃ የሚቀመጠውን የእለት እለት የአምልኮ መጽሃፍ የራፕሶዲ ኦፍ ሪያሊቲስ ደራሲ ናቸው፡፡ በመልእክታቸው ወደ በርካታ ልቦች የመለኮታዊ ህይወት እውነታን በማምጣት፣ እጅግ የተሰጡ የእግዚአብሄር ቃል አገልጋይ ናቸው፡፡

የእግዚአብሄርን መለኮታዊ መገኘት ወደ እያንዳንዱ ሰው ቤት የሚያደርሰው፣ "አትሞስፌር ፎር ሚራክልስ" (የተአምራት ከባቢ) የተሰኘው የቴሌቪዥን ፕሮግራም በሚሊዮን የሚቆጠሩ ሰዎችን ህይወት ነክቷል፡፡ የላቭ ወርልድ ሳተላይት ቴሌቪዥን መረብን በመጠቀም፣ የእርሳቸው የቴሌቪዥን ፕሮግራም ለዓለም ሁሉ የክርስቲያን ፕሮግራሞችን ለማዳረስ ችሏል፡፡

በዓለም በታወቀው የሂሊንግ ስኩል (የፈውስ ትምህርት ቤት)፣ የኢየሱስ ክርስቶስን የፈውስ ስራዎች በመግለጥ፣ እና ብዙዎች በመንፈስ ቅዱስ የስጦታ ስራ አማካኝነት ፈውስን እንዲቀበሉ ረድተዋል፡፡

ፓስተር ክሪስ በእግዚአብሄር መገኘት የዓለምን ህዝብ ለመድረስ ያላቸው ፍቅር ጥልቅ ሲሆን፣ በተለያዩ የማዳረስ ዘመቻዎች፣ የወንጌል ስርጭት ፕሮግራሞች እና በሌሎች በርካታ መድረኮች በሚሊዮን የሚቆጠሩ ሰዎች በእግዚአብሄር ቃል ድል አድራጊና ዓላማ ያለው ህይወትን እንዲለማመዱ በማድረግ ከሰላሳ ዓመታት በላይ መለኮታዊ ተልእኮአቸውን ተወጥተዋል፡፡

LoveWorld Publishing

# ማስ ወሻ

AMHARIC

# ማስ ወሻ

# ማስ ወሻ